# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት



## በትምህርት ሚኒስቴር በመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚገኙ ተማሪዎች ላይ የሚታዩ የሥነ-ምግባር ችግሮች እንዲሁም የሚገጥሟቸው ተቋማዊ እና አካባቢያዊ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ጥር 2005 ዓ.ም.

## ማውጫ

ገጽ


ክፍል አንድ ........................................................................ 1

መግቢያ ........................................................................ 1

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ ........................................................................ 2

የሚኒስቴር መ/ቤቱ አላማ (ተልዕኮ) ........................................................................ 2

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር ........................................................................ 2

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል አደረጃጀት ........................................................................ 3

የፋይናንስ ምንጭ ........................................................................ 4

የኦዲቱ አላማ ........................................................................ 5

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ........................................................................ 5

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርት ........................................................................ 6

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........................................................................ 6

ክፍል ሁለት ........................................................................ 8

ግኝቶች ........................................................................ 8

ለመምህራንና ተማሪዎች የሚያገለግል የሥነ-ምግባር ደንብና መመሪያን በተመለከተ፣ ........................................................................ 8

መምህራን የሚጠበቅባቸውን ተግባርና ኃላፊነት መወጣታቸውን በተመለከተ፣ ........................................................................ 11

ከመደበኛ ትምህርት በተጨማሪ የሚሰጠውን የማጠናከሪያ ትምህርት(ቲቶሪያል ክላስ) በተመለከተ፣ ........................................................................ 14

የኢኮኖሚ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የተዘጋጀ የመመልመያ መስፈርት ስለመኖሩና ተግባራዊ ስለመደረጉ፣ ........................................................................ 16

ጾታን ያማከሉ የሥነ-ልቦና አማካሪዎች ስለመኖራቸው፣ ........................................................................ 17

የሥነ-ምግባር፣ የሥርዓተ-ጾታና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤቶች ስለመኖራቸውና አገልግሎታቸው የተሟላ ስለመሆኑ፣ ........................................................................ 19

ሴት ተማሪዎችን ለሴትኛ አዳሪነት ተግባር አሳልፈው የሚሰጡ ደላሎች ስለመኖራቸው፣ ........................................................................ 20

ለተማሪዎች በቂ የመዝናኛና የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት ስለመኖራቸው፣ ........................................................................ 22

የቅንጅት ሥራና የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ስለመኖሩ፣ ........................................................................ 24

የተማሪዎች መኖሪያ/ዶርም/ና የዩኒቨርስቲዎቹን ቅጥር ግቢ ሁኔታ በተመለከተ፣ ........................................................................ 26

ተማሪዎች ሊደርስባቸው ከሚችሉ አካባቢያዊ ተፅዕኖ ለመከላከል ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የቅንጅት ስራ በተመለከተ፣ ........................................................................ 29

በየዩኒቨርስቲዎቹ መግቢያ በርና በየአገልግሎት መስጫ (ቢሮዎች) አካባቢ አቅጣጫ ጠቋሚ ስሌዳ መኖሩንና፣ ተማሪው አገልግሎት በሚያገኝበት ቦታ የሀሳብ መስጫ ሳጥን መቀመጡን በተመለከተ፣ ........................................................................ 34

ክፍል ሦስት ...................................................................................................................................36
የመደምደሚያ ሀሳቦች ......................................................................................................................36
ክፍል አራት ...................................................................................................................................38
የማሻሻያ ሀሳቦች ...........................................................................................................................38

**አባሪዎች**

- አባሪ 1 የትምህርት ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር /2003 ዓ.ም/
- አባሪ 2 የኦዲት መገምገሚያ መስፈርቶች
- አባሪ 3 በኦዲቱ ወቅት የተከለሱ መረጃዎች

# በትምህርት ሚኒስቴር

# በመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚገኙ ተማሪዎች ላይ የሚታዩ የሥነ-ምግባር ችግሮች እንዲሁም የሚገጥሟቸው ተቋማዊ እና አካባቢያዊ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

## ክፍል አንድ

### መግቢያ

1. ከፍተኛ ትምህርት በ1997 ዓ.ም ከነበረው 78,232 የመጀመሪያ ዲግሪ መደበኛ ተማሪዎች ብዛት በ2004 ዓ.ም ወደ 418,965 አድጓል፡፡ በተጠቀሰው ዓመት 24% የነበረው የሴቶች ተሣትፎ በ2004 ዓ.ም ወደ 28.6% አድጓል፡፡ በ1997 የድህረ ምረቃ መደበኛ ተማሪዎች ብዛት 3,604 የነበረ ሲሆን በ2004 ዓ.ም ግን ወደ 22,804 አድጓል፡፡ የሴት ተማሪዎች ድርሻ ከ9% ወደ 20.2% አድጓል፡፡

2. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዋነኛ ትኩረት የትምህርት ጥራትና አግባብነትን ማረጋገጥ ሲሆን፣ እ.ኤ.አ. በ1995 በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ሀያ ከተሞችና በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች የተደረገ ጥናት እንደሚያመለክተው ጫት፣ አልኮል፣ ቶባኮ፣ ሀሺሽ፣ ካናቢስ እና ሌሎች ሱስ የሚያሲዙ አደገኛ ዕጾችንና መድሀኒቶችን የመጠቀም ሁኔታ በተለይ በወጣቶችና ተማሪዎች ዘንድ እየተባባሰ መምጣቱ ታውቋል፡፡ (ምንጭ፡-የትምህርት ሚኒስቴር 2003-2007 ስትራቴጂክ እቅድ ገጽ 45 )

3. የአደገኛ ዕጽ ወይም መድኃኒት ሱሰኞች አንድን ዕጽ ወይም መድኃኒት በመጠቀም ብቻ እንደማይወሰኑና ሌሎችን ሱስ አስያዥ ነገሮችን ወደ መጠቀም እንደሚሄዱ፣ በተጨማሪም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎች ጥንቃቄ ለጎደለው የግብረ-ሥጋ ግንኙነትና ለጾታዊ ጥቃት የተጋለጡ መሆኑን ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡ ችግሩም ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ይዘት እንደሚኖረውና ውስብስብ እንደሆነ አፋጣኝ እርምጃም እንደሚያስፈልገው በጥናቱ ተመልክቷል፡፡ ችግሩ በተለይ ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ወረርሽኝ ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት ያለው መሆኑንና ሴት ተማሪዎችም ላልተፈለገ እርግዝናና ውርጃ እንደሚጋለጡ ተገልጿል፡፡

4. ይህ አሳሳቢ ችግር በተለይ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ደረጃ በፍጥነት እየተዛመተ እንደሆነ ተጠቅሷል። ይህ ደግሞ ተቋማቱ የሚፈለገውን ያህል የተማረና በሥነ-ምግባር የታነጸ ጥሩ ዜጋ ለማፍራት የሚያደርጉትን ጥረት ከማደናቀፋም በላይ ተተኪው ትውልድ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል።

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ

5. ብቁ ዜጋ የሚያፈራ፣ ጥራትና ፍታሀዊነትን ያረጋገጠ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት እስከ 2012 ሙሉ በሙሉ ገንብቶ መገኘት ነው።

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ አላማ (ተልዕኮ)

6. የትምህርት ዘርፉን የማስፈጸም አቅም በመገንባት፣ የብቃት መለኪያዎችን በማውጣትና በማስጠበቅ፣ ደረጃውን የጠበቀ የከፍተኛ ትምህርት በማስፋፋትና ተግባሮችን በአህዝቦት ሥራ በማገዝ ጥራት ያለው ውጤታማ፣ ፍትሀዊና አሳታፊ የትምህርት ስልጠና ሥርዓት ማረጋገጥ እና ህገ መንግስቱ ለዜጎች የሰጠውን መብትና ግዴታ የሚያከብሩና የሚያስከብሩ፣ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችላቸውን አቅምና ፍላጎት ለማዳበር የሚተጉ፣ ለዲሞክራሲ ግንባታና እንዲሁም ለሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገትና ሥርጸት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መልካም ዜጎችን ማፍራት ነው።

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

7. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 691/2003 መሰረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል:-
    - የትምህርትና ሥልጠና ስታንዳርድ ያወጣል፣ በሥራ ላይ መዋሉንም ያረጋግጣል፣ሀገራዊ የብቃት ማዕቀፍ ያዘጋጃል፣
    - አጠቃላይ የሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ ያዘጋጃል፣
    - የመምህራንን አነስተኛውን የትምህርት ብቃት መለኪያ ያወጣል፣
    - የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ሊያሟሉ የሚገባቸውን አነስተኛውን ደረጃ ያወጣል፣
    - የከፍተኛ ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣ በበላይነት ይመራል፣

- በየደረጃው ጥራትና አግባብነት ያለው ትምህርትና ሥልጠና መሰጠቱን ያረጋግጣል፣
- የሀገሪቱን የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲና ሥርዓተ ትምህርት መሠረት ያደረጉ ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ያዘጋጃል፣ ያስተዳድራል፣ የውጤት ሪኮርዶች ይይዛል፣ የውጤት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣
- የሀገሪቱን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂን ይቀርጻል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፣
- የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቅበላና ምደባ አፈጻጸም ፍትሃዊ መሆኑን ያረጋግጣል፣
- ትምህርትና ሥልጠናን በተመለከተ ሀገራዊ የአሕዝቦት ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

8. በተጨማሪም እያንዳንዱ ሚኒስቴር መ/ቤት በስራው መስክ፦
    - ፖሊሲዎችንና ሕጎችን ያመነጫል፣ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤
    - የፌዴራል መንግስቱ ሕጎች በስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
    - የጥናትና ምርምር ተግባሮችን ያከናውናል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀነባብራል፣ ያሰራጫል፤
    - የአቅም ግንባታ ስራዎችን ያከናውናል፤
    - ለክልሎች እንደ አስፈላጊነቱ ድጋፍና ምክር ይሰጣል፤ እንዲሁም ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር አስተባባሪነት የተቀናጀ ድጋፍ ያደርጋል፤
    - በህግ መሰረት ውሎችንና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ያደርጋል፤
    - ስለሥራው ክንዋኔ በየወቅቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል አደረጃጀት

9. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲሆን፣ በአንድ ሚኒስትርና በሶስት ሚኒስትር ዴኤታዎች ስር ባሉ በሶስት ዋና ዋና የሥራ ዘርፎች ላይ ትኩረት በማድረግ የሚንቀሳቀስ ነው፡፡ እነዚህም የሥራ ዘርፎች የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ እና የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በሚኒስቴር መ/ቤቱ 673 ቋሚ 31 ኮንትራት በድምሩ 704

ሠራተኞች እንዲኖረው የተፈቀደ ሲሆን በግንቦት 2004 ዓ.ም 553 ቋሚና 23 ኮንትራት በድምሩ 576 ሠራተኞች እንዳሉት ታውቋል፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡

10. ከላይ ከተጠቀሱት የሥራ ዘርፎች መካከል የኦዲቱ አካባቢ የሚመለከተው የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍን ሲሆን በሥሩ አምስት ንዑሳን ዘርፎች አሉት፡፡ እነሱም የኢትዮጵያ ኢጁኬሽናል ሪሰርች ኔትወርክ ዳታ ሴንተር፣ የከፍተኛ ትምህርት አቅም ግንባታ ዴስክ፣ ዩኒቨርስቲዎች፣ የትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል እና የትምህርትና ስልጠና ጥራት ማረጋገጫ ኤጀንሲ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ዘርፍ 29 ቋሚ እና 10 ኮንትራት በድምሩ 39 ሠራተኞች እንዲኖረው የተፈቀደ ሲሆን፣ 25 ቋሚና 9 ኮንትራት በአጠቃላይ 34 ሠራተኞች በግንቦት 2004 ዓ.ም. እንዳለው ታውቋል፡፡

## የፋይናንስ ምንጭ

11. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የገቢ ምንጭ ከመንግሥት የሚመደብ በጀት ብቻ ሲሆን የገቢና የወጪ መግለጫው በሰንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ | ገቢና ወጪ | 2002ዓ.ም. | 2003ዓ.ም. | 2004ዓ.ም. |
|---|---|---|---|---|
| 1. | መደበኛ በጀት | ብር 41,194,172.00 | ብር 60,658,787.00 | ብር 176,945,628.05 |
| 2. | ካፒታል በጀት | ብር 2,955,943,561.00 | ብር 4,272,837,851.00 | ብር 2,525,528,783.33 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **ብር 2,997,137,733.00** | **ብር 4,333,496,638.00** | **ብር 2,702,474,411.38** |
| 4. | መደበኛ ወጪ | ብር 27,333,971.84 | ብር 40,829,912.76 | **ብር70,407,788.93 (ከሐምሌ/03-መጋቢት/04)** |
| 5. | ካፒታል ወጪ | ብር 2,552,847,784.59 | ብር 3,250,530,216.83 | **ብር 1,294,796,396.75 (ከሐምሌ/03-መጋቢት/04)** |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **ብር 2,580,181,756.43** | **ብር 3,291,360,129.59** | **ብር 1,365,204,185.68** |

## የኦዲቱ አላማ

12. ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገቡ ተማሪዎች፣ ከአካዳሚክ ትምህርት ጐን ለጐን ደህንነታቸው የተጠበቀ፣ በሥነ-ምግባር የታነፁ፣ ኃላፊነት የሚሰማቸው፣ ሀገራዊ ራዕይ ያላቸው፣ ራሳቸውን ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና ከተለያዩ ሱሶች የጠበቁ፣ ብቁና መልካም ዜጋ ሆነው እንዲወጡ ይጠበቃል፡፡ ይሁን እንጂ የሚጠበቀው ውጤት ስኬታማ እንዳይሆን በተቋማቱ ውስጥና ውጭ በርካታ ችግሮችና አሉታዊ ተጽዕኖዎች ይገጥሙአቸዋል፡፡ ስለሆነም የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በትምህርት ሚኒስቴር በመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚገኙ ተማሪዎች ላይ የሚታዩ የሥነ-ምግባር ችግሮች እንዲሁም የሚገጥሟቸው ተቋማዊ እና አካባቢያዊ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቅረፍ የተዘረጋ የአሰራር ሥርዓት መኖሩንና ተፈፃሚ መደረጉን ማረጋገጥ ሲሆን በዚህ ጉዳይ ላይ የአሠራር ግድፈቶች ካሉ መንስኤያቸውን ለይቶ በማውጣትና የማሻሻያ ሀሣብ በመስጠት ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተሻለ አሰራር እንዲኖራቸው እገዛ ለማድረግና የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤትን የክዋኔ ኦዲት ዓላማ ለማሳካት ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

13. ከላይ የተመለከተውን የኦዲቱን ዓላማ ለማሳካት ለተከናወነው ኦዲት ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተዋል፡፡ እነርሱም:-
    1. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በተማሪዎች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ችግሮችን ለማስቀረት አስገዳጅና ተጠያቂነትን የሚያጠናክሩ ፖሊሲዎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ሊወጡ፣ ለሌላው ተቋም አስተማሪ እንዲሆኑ የየዩኒቨርስቲዎቹ ደካማና መልካም ተሞክሮ መረጃዎች ሊሰባሰቡ፣ ሊጠናቀሩና ሊሰራጩ የሚችሉበትና የመረጃ ልውውጥ የሚኖርበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፣
    2. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በዩኒቨርስቲ ግቢ ውስጥ ሊደርሱባቸው ከሚችሉ ማህበራዊ፣ ተቋማዊ፣ ሥነ-ልቦናዊና ጾታዊ ችግሮች ለመታደግ የሚጠበቅባቸውን ተግባርና ኃላፊነት እየተወጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
    3. በየትምህርት ተቋማቱ የሚገኙ የሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤቶች ሴት ተማሪዎች አግባብ ባልሆነ መንገድ ገቢ ለማግኘት ሲሉ ለአደጋ እንዳይጋለጡ የኢኮኖሚ ድጋፍ ማግኘት

ለሚገባቸው የገንዘብ ድጋፍ በማድረግና በአካዳሚክ ትምህርታቸው ወደ ኋላ ለቀሩ ከትምህርት ሰዓት ውጭ የማጠናከሪያ ትምህርት በመስጠት አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ መደረጉን ማረጋገጥ፣

የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርት

14. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሲሆን፣ ከላይ የተጠቀሱትን ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ኦዲት ለማድረግ እንዲያስችል 53 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የተመረጡት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና መመዘኛ መስፈርቶች ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ተልከው አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል፡፡ የተዘጋጁት መመዘኛ መስፈርቶች ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዞ ቀርቧል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

15. ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2002-2005 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ድረስ የተከናወኑ ሥራዎችን ነው፡፡ ኦዲቱ የተከናወነው በዋነኛነት በትምህርት ሚኒስቴር ሲሆን፣ በኦዲት አካባቢው ዙሪያ ከሰሩ በፌዴራል ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት እና በሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት ከተጠኑ ጥናቶች፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሥርዓተ-ጾታ፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስና የሥነ-ምግባር ጽ/ቤቶች በተገኙ የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች እና ሌሎች ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች በመሰብሰብና በመከለስ ለኦዲቱ መሠረት እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡

16. በተጨማሪም ለኦዲቱ ስራ በናሙና በተመረጡ 4 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማለትም በዲላ፣ በሀዋሳ፣ በጎንደርና በባህር-ዳር በሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ለሚገኙ ለሥርዓተ-ጾታ፣ ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ለሥነ-ምግባር ጽ/ቤቶች፣ ለተማሪዎች ህብረት፣ ለተማሪዎች ዲን፣ ለሥነ-ልቦና አማካሪዎች (በተገኙበት ዩኒቨርስቲ)፣ ለፕሮክተሮች (ለመኝታ ቤት ተቆጣጣሪዎች)፣ ለየተቋማቱ ፖሊስ አካላት እና ለፕሬዘዳንቶች እንዲሁም ከውጪ ባለድርሻ አካላት፣ ዩኒቨርስቲዎቹ ለሚገኙበት ከተማ አስተዳደርና ፖሊስ መምሪያ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና ከየኃላፊዎቹ የተገኙ ከኦዲት አካባቢው ጋር

ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች በመሰብሰብና በመከለስ፣ ለተማሪዎችና መምህራን መጠይቆችን በማስሞላትና ለተሰጡ መልሶች ትንተና በመስራት እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥና በዙሪያቸው ያሉትን ችግሮች በአካል ተገኝቶ በማየት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

# ክፍል ሁለት

# ግኝቶች

## ለመምህራንና ተማሪዎች የሚያገለግል

## የሥነ-ምግባር ደንብና መመሪያን በተመለከተ፣

17. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ለሚገኙ መምህራንና ተማሪዎች የሥነ-ምግባር ደንብና የዲሲፕሊን መመሪያ ሊዘጋጅ፣ ግንዛቤ ሊሰጥበትና ስለተግባራዊነቱም ክትትል ሊደረግበት ይገባል፡፡

18. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በዲላ፣ በሀዋሳ፣ በጎንደርና በባህር-ዳር ዩኒቨርስቲዎች የመምህራን የሥነ-ምግባር ደንብ እንደሌለ የተማሪዎች ደንብና መመሪያ ቢኖርም ግንዛቤውን ያላገኙ ተማሪዎች መኖራቸውንና በትክክል እየተተገበረም እንዳልሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

19. በተጨማሪም በአራቱም ዩኒቨርስቲዎች መጠይቅ ሞልተው ከመለሱት አብዛኛው መምህራን የሥነ-ምግባር ደንቡ እንዳልተዘጋጀ ወይም መኖሩን እንደማያውቁ እንዲሁም መጠይቅ ሞልተው ከመለሱት ተማሪዎች የሥነ-ምግባር ደንብና መመሪያ ቢኖርም ግንዛቤው የሌላቸው ተማሪዎች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

20. የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችም ተጠይቀው በሰጡት መልስ በዲላና በሀዋሳ የተማሪዎች የሥነ-ምግባር ደንብ አተገባበር ላይ የዲስኘሊን ኮሚቴው ውሳኔ መዘግየትና ጭራሽ እርምጃ አለመውሰድም ስላለ ተማሪው ለመጥፎ ሥነ-ምግባር እንደሚበረታታ፣ (የየዩኒቨርስቲው ኘሮክተር ኃላፊዎች) ሀዋሳ አካባቢው ጫት የሚመረትበት በመሆኑና ተማሪው በሰዓቱ ይግባ ለማለት በዙሪያው ያለው አጥር ክፍት በመሆኑ ለጥበቃ ስለሚያስቸግር ችግሩን ማቆም እንዳልተቻለና በግንባታ ሠራተኞች በኩል ጫት ወደግቢው እየገባ ተማሪው በስፋት ሲጠቀምባቸው እንደሚታይ፣ (የሥርዓተ-ጾታ ኃላፊ) አጥር ባለመኖሩም ምክንያት የተቀጡና ግቢ እንዳይገቡ የተከለከሉ ተማሪዎች ገብተው እንደሚገኙ፣ አጥር ለማጠር ጨረታ ወጥቶ ያሸነፈው አካል በፍጥነት ለማጠር

እንዳልተቻለ፣ (የተማሪዎች አገልገሎት ኃላፊ) በ2004 ዓ.ም. ሀሽሽ ይዘው የተገኙ ተማሪዎች ተይዘው ለፍርድ ቤት እንደቀረቡና በ2005ም ይዘው የተገኙ ተማሪዎች እንዳሉ፣(የሀዋሳ ፖሊስ መምሪያ ኃላፊ) እንዲሁም በባህር-ዳር በአሁን ሰዓት ኘሮፖዛል ተቀርጾ የተጠናቀቀና የጥበቃ ኃይሉን በማጠናከር ሥራ እየሰሩ እንደሆነ ነገር ግን ችግሩ ሥር የሰደደ በመሆኑ በሂደት እንደሚስተካከል (የተማሪዎች አገልግሎት ኃላፊ)፣ በሀዋሳ በጎንደርና በባህር-ዳር እርቃንን የሚያጋልጡ አለባበስ ያላቸው ሴት ተማሪዎች እንዳሉና በሀዋሳ በአለባበስ ላይ የወጣ ረቂቅ የሥነ-ምግባር ደንብና መመሪያ ቢኖርም በባህር-ዳርና በጎንደር  ህጉ እንዳልወጣ (የየዩኒቨርስቲው የዶርም ተቆጣጣሪዎች)
ገልጸዋል፡፡



ፎቶ 1፣ በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ዋናው ግቢ በግቢው ፖሊስ ከተማሪ ላይ የተያዘ ሀሺሽ

21. ስለጉዳዩ የየዩኒቨርስቲው ኃሬዘዳንቶች ተጠይቀው ከሰጡት መልስ ለመረዳት እንደተቻለው፣ በዲላ  የመምህራን ሥነ-ምግባር ደንቡ እንደሌለና አለመኖሩ ኢ-ፍታሐዊነትን ሊያስከትል እንደሚችል፣ የተማሪዎቹም ዩኒቨርስቲው በወቅቱ የሥነ-ምግባር ደንቡን የማድረስና ተማሪውም ቢሆን ግዴታን አውቆ የመፈፀም ችግር እንዳለ፣

በሀዋሳ የመምህራን የሥነ-ምግባር ደንብና መመሪያውን ለማዘጋጀት መረጃን እያሰባሰቡ እንደሆነና ነገርግን ከላይ ባለው አካል ሁሉንም ዩኒቨርስቲዎች በሚያጠቃልል መልኩ ቢዘጋጅ የተሻለ እንደሚሆን፣

በጎንደር በሁሉም ዩኒቨርስቲ የሚተገበር አገር አቀፍ የሆነ ደንብና መመሪያ እንዲኖር ካልተደረገ በስተቀር ያጠፋ መምህር በዲሲፒሊን ኮሚቴ ጉዳዩ ታይቶ ሲቀጣ ጥሎ ሊሔድ የሚችልበት ሁኔታ እንዳለና የተማሪዎችን አለባበስም በተመለከተ ህግ ማውጣት የተማሪውን መብት መጋፋት በመሆኑ አገራዊ እይታ ያለው ለሁሉም ወጥ የሆነ ተማሪዎች የሚመሩበት ህግና ደንብ ካልወጣ በስተቀር በዩኒቨርስቲ ደረጃ ማውጣት ተማሪው ከሌሎች ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ጋር የመረጃ ልውውጥ ስለሚኖረው መብቱን እንደተገፈፈ ቆጥሮ እንደሚያስቸግር፣

በባህር-ዳር አለባበስን በተመለከተ ጊዜው የአለም-አቀፋዊነት (Globalization) እንደመሆኑ ተማሪዎቹ የትም ሄደው የሚሰሩ በመሆናቸው የግል አቋማቸው የፈለጉትን አይነት ይልበሱ የሚል እንደሆነ፣

ገልጸዋል፡፡

22. ስለጉዳዩ ለትምህርት ሚኒስቴር በተላከው ነባራዊ ሁኔታ ላይ በተሰጠው መልስ እያንዳንዱ ዩኒቨርስቲ ሌጅስሌሽን /ውስጠ ሕገ-ደንብ/ እንዳለው፣ ሌጅስሌሽኑ የመምህራንን ዲሲፕሊን ጨምሮ በርካታ ጉዳዮችን የያዘና በስራ ላይ የዋለ ሰነድ መሆኑን፣ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ የመንግስት ሰራተኞች ደንብም ለመምህራንም ጭምር እንደሚሰራ፣ በተጨማሪም በሁሉም ዩኒቨርስቲዎች እየተሰራበት ያለ Harmonized Acadamic Policy የመምህራንንና የተማሪዎችን አካዳሚክ ጉዳዮች የሚያካትት መሆኑና በእነዚህ ደንቦችና መመሪያዎች የማይካተት የመምህራን ጉዳይ ይኖራል ተብሎ ስለማይታመን የመምህራንን የስነ-ምግባርና የዲሲፕሊን ደንብ የሚለውን መቀበል እንደሚቸገሩ ገልጸዋል፡፡

23. ሆኖም ከላይ የተገለጹት የመምህራንን ስነ-ምግባር ጉዳይ የተመለከቱ ሰነዶች መኖራቸው በትምህርት ሚኒስቴር ቢገለጽም በናሙና በታዩ ዩኒቨርስቲዎች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎችና መምህራን ለቀረበው ቃለ-መጠይቅና መጠይቅ በተሰጠው መልስ ላይ ስለሰነዶች አለመጠቀሱ ሰነዶቹ በሁሉም ዩኒቨርስቲዎች አለመኖራቸውን ወይም በሁሉም ዩኒቨርስቲዎች ኖረው የግንዛቤ ክፍተት መኖሩን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም የመምህራን ስነ-ምግባር ደንብና መመሪያ ቢኖር መምህሩ ባለሙያ በመሆኑ በፈጸመው የዲሲፒሊን

ግድፈት የትም ቦታ ቢሔድ የሚጠየቅበት በመሆኑ አስፈላጊነቱ አጠያያቂ አይደለም፡፡ የተማሪዎች የሥነ-ምግባር ደንብንም በተመለከተ ግንዛቤውን ያላገኙ አንዳንድ ተማሪዎች መኖራቸው የትግበራ ሥራው ላይ ክፍተት የሚፈጠር በመሆኑና በተማሪዎች አለባበስ ላይም ወጥ የሆነ የስነ-ምግባር ደንብ አለመውጣቱ (በሀዋሳ ረቂቅ የሥነ-ምግባር ደንቡ ላይ ተካቷል) ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

## መምህራን የሚጠበቅባቸውን ተግባርና ኃላፊነት መወጣታቸውን በተመለከተ፣

24. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ተማሪዎች በክፍል መገኘታቸውን ለማረጋገጥ የክፍል መቆጣጠሪያ (class attendance) በወጥነት ሊይዙና እራሳቸውም በተሠጣቸው ክፍለ-ጊዜ መሰረት በክፍል ሊገኙ፣ የተማሪዎችን ውጤት በማስታወቂያ ቦርድ ላይ ከመለጠፋቸው በፊት የፈተና ውጤታቸውንና ተያያዥነት ያላቸውን የመመዘኛ ሰነዶች ሊያሳዩዋቸውና ቅሬታም ካለ በግልጽ ሊያነጋግሩአቸው እንዲሁም ፈተናን እንደ መቅጫ መሳሪያ የሚጠቀሙ፣ ውጤት አሰጣጣቸው አድሎአዊ የሆነ፣ ሴት ተማሪዎችን ለውጤትም ሆነ ለተለያዩ የትምህርት ተግባራት ወሲብን እንደቅድመ ሁኔታ የሚጠይቁ መምህራን ከተገኙ ተገቢ እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡

25. ይሁንና በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ካምፓሶች ከተሰበሰበው መረጃ፡-
    ሰዓት አርፍደው ክፍል የሚገቡና የሚቀሩ፣ ፈተና ላይ አይመጣም በማለት ከተማሪው ጋር ተስማምተው የሴሚስተሩን ኮርስ ሳያጠናቅቁ ፈተና የሚሰጡ፣ በወቅቱ በስራ ገበታቸው ላይ ሳይገኙ ቀርተው የፈተና ወቅት ሲደርስ በአጭር ጊዜ ኮርሱን አጠናቀው ፈተና የሚሰጡ፣ የተማሪውን የፈተና ውጤት በወቅቱ የማያሳውቁ፣ (በተለይ ተማሪዎቹ የመጨረሻ ውጤታቸውን የሚያዩት ከእረፍት ሲመለሱ መሆኑ) ተማሪው በትምህርት ገበታው ላይ መገኘቱን የማያረጋግጡ (Class Atendance የማይዙ)፣ ፈተናን እንደ መቅጫ መሳሪያ የሚጠቀሙና ውጤት አሰጣጣቸው አድሎአዊ የሆነ እንዲሁም ለውጤት አሰጣጥ ሴት ተማሪዎችን የወሲብ ጥያቄን እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚያቀርቡ አንዳንድ መምህራን መኖራቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

26. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች በሴት ተማሪዎች ላይ ወሲባዊ ጥቃት የሚያደርሱ፣ ለተማሪዎች በወቅቱ ውጤት የማያሳዩ፣ ፈተናን እንደ መቅጫ መሳሪያ

የሚጠቀሙና አድሎአዊ ውጤት አሰጣጥ ያላቸው መምህራን መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ የተከለሰው መረጃ በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡

27. እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የየዩኒቨርስቲዎቹ የስራ ኃላፊዎች በጉዳዩ ላይ በሰጡት መልስ፣

በዲላ ውጤት ሳያዩ ክረምት ላይ ሄደው ተመልሰው ሲመጡ ውጤታቸው የማያስቀጥል ሲሆን ተመልሶ ለመሄድ ችግር ስለሚገጥማቸው በየቡና ቤት እንደሚገቡና ለተለያየ ችግር እንደሚጋለጡ፣(የፕሮክተር ኃላፊዎች)

መምህራን የውጤት ጥያቄን የሚያስተናግዱበት ሁኔታ እንደሌለና የተማሪ ህብረቱ ይህን ችግር ቢያቀርብም የበላይ ኃላፊዎች ችግሩን ለመፍታት ክትትል እንደማያደርጉ፣ (የተማሪዎች ህብረት ኃላፊዎች)

ከመሄዳቸው በፊት ውጤታቸውን የማያውቁ ተማሪዎች እንዳሉና ወጪ አውጥተው ከመጡ በኋላ በውጤት ማነስ ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ የሚደረግበት ሁኔታ መኖሩን እንዲሁም በሞባይል መልዕክት እየላኩ ቅድመ ጥያቄ የሚያቀርቡ በቁጥር የሚገለፁ ጥቂት መምህራን መኖራቸውን፣ (የሥነ-ምግባር ጽ/ቤት አስተባባሪ)

በሀዋሳ በአሁኑ ሰዓት አብዛኛው መምህራን የፈተና ውጤት እንደማያሳዩና ለሴቶች መጠቃት ትልቁ ችግር ይህ ነው የሚል እምነት እንዳላቸው፣ ለወደፊት መስተካከል ያለበት ሁኔታም እንዳልተመቻቸ፣

መምህራን ለሚከታተሏቸው ተማሪዎች ውጤት አልተሰጠም /No-Grade/ የሚሰጡበት ሁኔታ ያለና ተማሪዎቹም ጋር ቀርቦ የመግለፅ ችግር እንዳለ፣ መረጃው ሲገኝ እርምጃ እንደሚወሰድ ይፋ የሚደረግበት ሁኔታ ግን ምቹ የሆነ የማስታወቂያ መለጠፊያ ባለመኖሩ እንደ ክፍተት የሚያዩት እንደሆነ፣ (የሥነ-ምግባር ጽ/ቤት ኃላፊ)

በጎንደር ከላይ የተገለጹትን የስነ-ምግባር ጉድለቶች የሚፈፅሙ መምህራን መኖራቸውን ሆኖም ራሳቸውን ደብቀው ስለሚሰሩ በቂ መረጃ ማግኘት ከባድ እንደሆነ፣ ዩኒቨርስቲው በርቀት በመገኘቱና ተመድበው የሚመጡ መምህራን አብዛኛውን ጊዜ ወጣቶች በመሆናቸው እውቀታቸውን ለወሲባዊ ትንኮሳ እንደ መሳሪያ እንደሚጠቀሙበት፣ ሴት ተማሪዎችም ጋ ጥቃቱን በመረጃ የማምጣት ችግር መኖሩንና ወደ 8 ዩኒቨርስቲዎች ለተሞክሮ በዞሩበት ያዩት የየተቋማቱ ትልቅ በሽታ ይሄ እንደሆነ፣ ተማሪውም ይህንን ጉዳይ እንዲያሳውቅ ለማበረታታት ህጋዊ ከለላ /ዋስትና/ እንደሌለው፣ ችግሩ ተከስቶም ወደ በላይ አካል ሲቀርብ ተገቢው ቅጣት እንደማይሰጥ፣ በተለይ በሰኔ ተማሪዎች ማለፋቸውንና

መውደቃቸውን ሳያውቁ ስለሚሄዱ ሲመለሱ ውጤታቸው ከተበላሸ ወደ ሀገራቸው ለመመለስ አቅም የሌላቸው እዚህ እየቀሩ ለአልባሌ ተግባር እንደሚጋለጡ፣ ሁሉም ባይሆኑም ኮርሱን የማይጨርሱ መምህራን እንዳሉና አንዳንድ መምህራን የግል ስራ ስለሚሰሩና የማስተማሩን ሥራ በባለቤትነት ስሜት ስለማይዙት ኮርሱ የማይጠናቀቅበት ሁኔታ እንዳለ፣ ባለመገኘታቸው ግን በአንድም መምህር ላይ የተወሰደ እርምጃ እንደሌለ፣ (የተማሪዎች መማክርት ኃላፊዎች)

በባህር-ዳር ውጤት የማያሳዩ መምህራን እንዳሉ በተለይ በሰኔ መጨረሻ ላይ ውጤቱን ሳያውቅ የሚሔድ ተማሪ መኖሩን፣ አንድ ተማሪ ሲወድቅ እንደገና የመፈተን መብት ቢኖረውም ተግባራዊ የማይደረግበት ሁኔታ እንዳለ፣ ውጤት ለመስጠት አድሎአዊ የሆኑና ጾታዊ ጥቃት የሚያደርሱ፣ ከአንድ ተማሪ ጋር ሲጣሉ የክፍሉን ተማሪ በሙሉ የሚቀጡ፣ በተከታታይ ክላስ የመገኘት ልምድ የሌላቸውና የቀሩበትን ጊዜ ለማካካስ ተማሪውን አጨናንቀው ኮርሱን የሚጨርሱ ወይም ሳይጨርሱ ፈተና የሚያወጡ መምህራን መኖራቸውንና እርምጃም ለመውሰድ የመረጃ ክፍተትና ጉዳዩን ይዞ መከታተሉ ላይ ችግር እንዳለ፣(የተማሪዎች መማክርት ኃላፊዎች)

ገልጸዋል፡፡

28. ስለጉዳዩ የየዩኒቨርስቲው ኘሬዘደንቶች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፡-

በዲላ በጉዳዩ ላይ መረጃ የማግኘት ችግር መኖሩንና መረጃው ሲገኝ የሚቀጡ መምህራን መኖራቸውን፣ የተማሪውንም ውጤት የተወሰኑ አስተማሪዎች እንደሚያሳዩና የማያሳዩም እንዳሉ ችግሩን ለመቅረፍ ቢ.ኤስ.ሲ እና ሞጁላራይዜሽን ተግባራዊ እንደሚደረግ፣ የጠበቀ ባይሆንም መምህራኑ አቴንዳስ መያዛቸውን ቁጥጥር እንደሚደረግና ሁለት ሦስት ክፍል ብቻ ገብተው ፈተና የሚሰጡ እንዳሉና ሥራው በደንብ እንዳልተሰራ፣ (የዲላ ዩኒቨርስቲ የአስተዳደር ልማት ም/ኘሬዝዳንት)

በሀዋሳ መረጃው ትክክል እንደሆነና በዚህ አመት በወቅቱ ውጤት በማያሳዩ መምህራን ላይ የዲስኘሊን እርምጃ እንዲወሰድ በሪጅስትራር ደብዳቤ የሚፃፍበት ሁኔታ እንዳለ የዚህ ውጤትም ዘንድሮ እንደሚታይ፣ በሥነ-ምግባር ዙሪያም እንደ ፍርድ ቤት በቂ ማስረጃ በመሰብሰብ ባይሄዱበትም በአንዳንድ መረጃዎች ላይ በመመርኮዝ በራሳቸው የሚወስዱት እርምጃ እንዳለና ለዩኒቨርስቲው ህብረተሰብ የሚል ግልባጭ እንደሚጻፍ ሆኖም ትኩረት ተሰጥቶት እንደማይለጠፍ ወደፊት ተማሪዎች ቦርድ ላይ መለጠፍ አለበት የሚል እምነት እንዳላቸው፣ በተለይ ትንሽ ተማሪ በክፍል ሲገኝ መምህራን አቴዳንስ የመያዝ ግዴታ

እንዳለባቸውና ተማሪዎችም የዚህ አይነት ችግር ሲኖር እንዲያሳውቁ ለማድረግ ግንዛቤውን መስጠት እንደሚያስፈልግ፣

በጎንደር ክስተቶቹ የማይካዱና ሆኖም ግን እየተሻሻለ የመጣ ጉዳይ እንደሆነ ሴት ተማሪዎችም ራሳቸው የሚከፍቱት በር መኖሩን መምህራኖቹ ወጣቶች በመሆናቸው እድሜም የሚፈጥረው ጉዳይ እንደሆነና ችግሩ መረጃውን ማግኘት እንጂ መረጃው ሲገኝ እርምጃ እንደሚወሰድ፣ ከየስራ ክፍሉ ጋር በየወሩ እየተገናኙ የአፈፃፀም ግምገማ የሚያደርጉበት ሥርዓት እንደዘረጉና ይህ ደግሞ ነገ ላይ ትልቅ መሻሻል ያመጣል የሚል ተስፋ እንዳለው፣

በባህር-ዳር ወሲብን እንደቅድመ ሁኔታ የሚጠይቁ እንዳሉ ግን ጥቂቶች እንደሆኑ ሆኖም በአጠቃላይ የቁጥጥር ሥርዓቱን እያጠናከሩና በተማሪዎች ህብረት በኩል እየተከታተሉ እንደሚገኙ የየዩኒቨርስቲው ኃሬዘዳንቶች ገልጸዋል፡፡

29. ሆኖም ከላይ የተገለጹትን የሥነ-ምግባር ግድፈቶች በሚፈጽሙ ሁሉም መምህራን ላይ በበቂ ክትትል እርምጃ አለመወሰዱና፣ ሲወሰድም የተወሰደው እርምጃ ለተቋሙ ማህበረሰብ ይፋ የሚደረግበት አሰራር አለመኖሩ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

## ከመደበኛ ትምህርት በተጨማሪ የሚሰጠውን የማጠናከሪያ ትምህርት(ቲቶሪያል ክላስ) በተመለከተ፣

30. የማጠናከሪያ ትምህርት አሰጣጡ ወጥነት እንዲኖረው ስለአሰጣጡ መመሪያ ሊዘጋጅ፣ ለማጠናከሪያ ትምህርት በተመረጡ ትምህርቶች/ኮርሶች/ ላይ ሞጁል ተዘጋጅቶ የትምህርት ድጋፉ በሞጅሉ መሰረት ሊሰጥ፣ በጠቀሜታው ዙሪያ በተማሪዎቹ ላይ የግንዛቤ ስራ ሊሰራ፣ መምህራን ከመደበኛው የማስተማሪያ ሰዓት ውጪ በተጨማሪ ሰዓት ለሚሰጡት የማጠናከሪያ ትምህርት ማበረታቻ ሊሰጣቸውና በአፈጻጸሙም ላይ የክትትልና የግምገማ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

31. ይሁንና በአራቱም ዩኒቨርስቲዎች በታዩ ካምፓሶች ከመደበኛ ትምህርት በተጨማሪ የሚሰጠውን የማጠናከሪያ ትምህርት (ቲቶሪያል ክላስ) በተመለከተ በተማሪዎችና መምህራን ተሞልቶ ከተመለሰው መጠይቅ፣

አሰጣጡ በሞጁል ያልተደገፈና መምህራን ባመቻቸው መልኩ የሚያስተምሩት መሆኑን፣ ለማጠናከሪያ ትምህርት ተብሎ የወጣ ቋሚ ክፍለ ጊዜ የሌለው፣ ፈተና ሊደርስ አካባቢ

የሚሰጥና መሰረታዊ እውቀት ከማስጨበጥ ይልቅ ፈተናን መሰረት ያደረገ መሆኑን፣ በተማሪዎችም መሰጠቱን፣ በሀዋሳ ማጠናከሪያ ትምህርቱ ለአንደኛ አመት ሴት ተማሪዎች ብቻ መሰጠቱን፣ የማጠናከሪያ ትምህርቱ የሚያስፈልጋቸውን ኮርሶች በወቅቱ የመለየት ችግር መኖሩን፣ የማጠናከሪያ ትምህርት ሲሰጥ የማይገኙ ተማሪዎች መኖራቸውና እንዲገኙ ለማድረግ ስለጠቀሜታው በቂ የግንዛቤ ስራ አለመሰራቱን እና የማጠናከሪያ ትምህርቱን ለሚሰጡ መምህራን በቂ ማበረታቻ አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

32. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት ከተከለሰው መረጃ፣

በማጠናከሪያ ትምህርት አሰጣጥ ሂደት ላይ የድጋፍና ክትትል ማነስ መኖሩን፣ የማጠናከሪያ ትምህርት አሰጣጥ በትምህርት ፖሊሲው የተካተተ ቢሆንም መምህራን የማጠናከሪያ ትምህሩቱን እንደ አንድ የሥራ አካል አድርገው አለማየታቸውን፣ ት/ቤቶች ከሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤት ጋር ተቀናጅተው ባለመሥራታቸው በማጠናከሪያ ትምህርት አሰጣጡም ሆነ የተማሪዎችን ተጠቃሚነትና ውጤታማነት ክትትል በመረጃ መለካት አለመቻሉንና ብዙ ሴት ተማሪዎች በተማሪ መማር ባለመፈለጋቸው ሥራው የተሣካ እንዳይሆን ማድረጉን፣ የኘሮግራም መጣበብና ቋሚ አለመሆን ችግር መኖሩን ለመረዳት ተችሏል፡፡ የተከለሰው መረጃ በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡

33. ስለጉዳዩ የየዩኒቨርስቲው የሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣

በዲላ የማጠናከሪያ ትምህርቱ የሚሰጠው የፈተና ወቅት ሲደርስ መሆኑንና የማጠናከሪያ ትምህርቱን ለሚሰጡ መምህራን ብር 100.00 ለተማሪዎች ብር 25.00 በሰዓት እንደሚሰጥ፣

በሀዋሳ የማጠናከሪያ ትምህርት የገንዘብ እጥረት በመኖሩ ለአዲስ ሴት ተማሪዎች ብቻ እንደሚሰጥ፣ በማጠናከሪያ ትምህርቱ ላይ የማይገኙ ተማሪዎች መኖራቸውንና አስተማሪዎችም ቦታው ላይ ተገኝቶ የማጠናከሪያ ትምህርቱን የመስጠት ችግር እንዳለ፣

በጎንደር ለማጠናከሪያ ትምህርት ሞጁል ዝግጅትና ለመምህራን የሚከፈል ቋሚ በጀት አለመኖሩንና የማጠናከሪያ ትምህርቱን የሚሰጡት መምህራን ካለክፍያ ለመስጠት ፍቃደኛ ባለመሆናቸው በተማሪ እንደሚሰጥ፣

በባህር-ዳር በሞጁላራይዜሽን ምክንያት ተማሪውም መምህሩም ጊዜ ስለሌለው የማጠናከሪያ ትምህርት መስጠት እንደሚያስቸግር ሆኖም ከትምህርት ሰዓት ውጪና ቅዳሜና እሁድ ጉበዝ ተማሪዎችን በመጠቀም እንዲረዱ እንደሚደረግና መምህራን የተለየ ጫና

ካልተፈጠረባቸው በስተቀር ክፍያ ስለማይከፈላቸው ለማስተማር ፍቃደኛ እንዳልሆኑ የሞጁል ዝግጅትም እንደሌለ፣
ገልጸዋል፡፡

34. እንዲሁም በዲላ የዩኒቨርስቲው የአስተዳደር ልማት ም/ኘሬዝዳንት የማጠናከሪያ ትምህርቱ የተጠናከረ አለመሆኑ እውነት እንደሆነ፣ ሞጁልም ለማጠናከሪያ ትምህርት እንደማይዘጋጅ፣ ቲቶሩን ለሚሰጡ መምህራንና ተማሪዎች የሚደረገውም ክፍያ በተቋሙ የተወሰነ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

35. በመሆኑም የማጠናከሪያ ትምህርትን በተመለከተ ስለአሰጣጡ በሁሉም ዩኒቨርስቲ የሚተገበር ወጥ መመሪያ አለመዘጋጀቱ ወጥ አሰራር እንዳይኖር የሚያደርገው በመሆኑና በአሰጣጡም ላይ በየዩኒቨርስቲው አመራሮች ትኩረት ተሰጥቶት አለመሰራቱ ተማሪዎቹ በማጠናከሪያ ትምህርት ተደግፈው የተሻለ ውጤት እንዳያስመዘግቡና የተሻለ ውጤት ለማምጣት ሲሉ ለተለያየ የሥነ-ምግባር ጉድለት እንዲጋለጡ ስለሚያደርጋቸው አሰራሩ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

## የኢኮኖሚ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የተዘጋጀ የመመልመያ መስፈርት ስለመኖሩና ተግባራዊ ስለመደረጉ፣

36. በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች የኢኮኖሚ ድጋፍ ለማድረግ የመመልመያ መስፈርት ተዘጋጅቶ መስፈርቱን የሚያሟሉ ተማሪዎች ብቻ ድጋፍ ሊደረግላቸውና አፈጻጸሙ ላይ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

37. ነገር ግን በኦዲቱ ወቅት በዲላ፣ በሀዋሳና በባህር-ዳር በሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች የኢኮኖሚ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ለሚሰጠው የኢኮኖሚ ድጋፍ የመመልመያ መስፈርት አለመኖሩ፣ ድጋፉ የሚሰጠውም ለሴት ተማሪዎች ብቻ መሆኑንና የኢኮኖሚ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ድጋፍ ማግኘት እንዲችሉ ለማድረግ የበጀት እጥረትና ፈንድ የማፈላለግ ችግር መኖሩ ታውቋል፣

38. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ድጋፍ ለሚሹ ሁሉም ተማሪዎች በአቅም ውስንነት የተነሳ የኢኮኖሚ ድጋፍ መስጠት አለመቻሉን ለመረዳት ተችሏል፡፡ መረጃው በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡

39. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የየዩኒቨርስቲው የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው፡-

በሃዋሳ ለመረዳት የሚመጡት ተማሪዎች የሚያመጡትን ማስረጃ እውነተኛነት ለማጣራት አስቸጋሪ መሆኑንና የኢኮኖሚ ድጋፍ ለማድረግ በቂ ገንዘብ ስለሌለ በጣም የበዛ ችግር አለባቸው የሚባሉ ተማሪዎችን ብቻ እንደሚረዱ፣

በባህር-ዳር የኢኮኖሚ ችግር ያለባቸውን ሁሉንም ተማሪዎች ለመደገፍ የበጀት እጥረት ማጋጠሙን፣

(የሐዋሳና ባህር-ዳር ዩኒቨርስቲዎች የሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤት ኃላፊዎች) እንዲሁም

በጎንደር ሴት ተማሪዎች የኢኮኖሚ ችግር ሲገጥማቸው ተጽዕኖውን ለማሸነፍ በእድሜ አቻ ካልሆኑ ወንዶች (ሹገር ዳዲዎች) ጋር ጾታዊ ግንኙነት የሚፈጥሩበት ሁኔታ መኖሩን፣ (የጎንደር ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ህብረት ኃላፊዎች)

ገልጸዋል፡፡

40. በመሆኑም የኢኮኖሚ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች የሚደረገው ድጋፍ የሚበረታታ ቢሆንም ድጋፉን ለመስጠት የሚያስችል በሁሉም ዩኒቨርስቲ የሚተገበር ወጥ የመመልመያ መስፈርት አለመኖሩ ችግሩ ጎልቶ የሚታይባቸው ተማሪዎች ቅድሚያ እንዳያገኙ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

## ጾታን ያማከሉ የሥነ-ልቦና አማካሪዎች ስለመኖራቸው፣

41. በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ሥነ-ልቦናዊ ችግሮች ሲገጥማቸው የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ጾታን ያማከሉ፣ ለሥራው ብቃትና ፍላጎት ያላቸው፣ ለማማከር አገልግሎት ብቻ የተመደቡ የሥነ-ልቦና አማካሪ ባለሙያዎች ሊኖሩ ይገባል፡፡

42. ይሁን እንጂ፣ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ ዩኒቨርስቲዎች በመገኘት ለማጣራት እንደተቻለው የሥነ-ልቦና አማካሪ ባለሙያ፡-

በዲላ በሶስቱም ካምፓሶች አለመኖሩ፣ በጎንደር የማራኪ ካምፓስ ቢሮው ከላይ ክፍት ስለሆነ አጠገቡ ላለው ቢሮ ድምፅ የሚያስተላለፍ በመሆኑ የሥነ-ልቦና አማካሪ ባለሙያዋ አገልግሎቱን ለመስጠት መቸገራቸው፣ በባህር-ዳር በፖሊ ካምፓስ የሚገኘው ባለሙያ ቢሮ የሌለውና በተማሪዎች አገልግሎት ፀሐፊ ቢሮ ውስጥ ተደርቦ የሚሰራ በመሆኑ አገልግሎቱን ለማግኘት የሚመጣ ተማሪ ሲኖር ሌላውን ሰራተኛ በማስወጣት እየሰራ ያለ መሆኑንና በጎንደር በማራኪ ካምፓስ ከምትገኘው አንድ የሥነ-ልቦና አማካሪ ባለሙያ በስተቀር በኦዲቱ በታዩት ዩኒቨርስቲዎች ሴት ባለሙያዎች አለመኖራቸው ታይቷል፡፡

43. ስለሁኔታው ጉዳዩ የሚመለከታቸው የየዩኒቨርስቲዎቹ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣

በዲላ በዋናውና በአዲሱ ካምፓስ በትርፍ ጊዜ የሚሰሩ የሳይኮሎጂ መምህራን እንዳሉና ለአዲስ ተማሪዎች በሚዘጋጀው በእንኳን ደህና መጣችሁ ፕሮግራም ላይ የሥነ-ልቦና ምክር እንደሚሰጡ፣ ሆኖም የሚሰጡት አገልግሎት በቂ እንዳልሆነ፣ (የአስተዳደር ልማት ም/ፕሬዝዳንት)

በጎንደር የአማካሪዎችን ጾታ በተመለከተ በተለይ ሴቶችን ባዮሎጂካል ችግር ሲገጥማቸው ለመርዳት ተመሳሳይ ጾታ ቢሆን እንደሚመረጥ፣ (የማራኪና የቴዎድሮስ የሥነ-ልቦና አማካሪዎች)

በባህር-ዳር በእርግጥ አማካሪዎች ሴቶች ቢሆኑ ኃላፊነትን ከመሸከምና ሚስጥር ከመጠበቅ አንፃር ጥሩ እንደሆነ ነገር ግን የስራ ማስታወቂያ ባወጡበት ጊዜ የመጡት ወንዶች መሆናቸውን ስለዚህ ወደፊት እንደሚታሰብበት፣ (የዩኒቨርስቲው የተማሪዎች አገልግሎት ኃላፊ) የቢሮው አቀማመጥ በራሱ ተማሪዎች ሚሥጥራቸው በማይባክንበት መንገድ መጥተው እንዳይገለገሉ እንዳደረገና ችግሩ መፍትሔ እንዲሰጥበት ተጠይቆ ምላሽ ያላገኘ መሆኑን፣ (የባህር-ዳር ዩኒቨርስቲ የሥነ-ልቦና አማካሪ ባለሙያዎች)

ገልጸዋል፡፡

44. እንዲሁም በተማሪዎች ተሞልቶ ከተመለሰው መጠይቅ የሥነ-ልቦና ችግር ቢገጥማቸው ተመሳሳይ በሆነ ጾታ መገልገል እንደሚፈልጉ የገለጹት ተማሪዎች በዲላ 32፣ በሀዋሳ 32፣ በጎንደር 25 እና በባህር-ዳር 33 በመቶ ናቸው፡፡

45. ስለጉዳዩ ለትምህርት ሚኒስቴር ተልኮ በተሠጠው የነባራዊ ሁኔታ መልስ በዲላ ሁለት ካምፓሶች አንዳንድ ባለሙያ መኖሩ ተገልጿል፡፡ ሆኖም በኦዲቱ ወቅት ቦታው ላይ በመገኘትና ለኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ አማካሪዎቹ አለመኖራቸው የተገለጸ ቢሆንም ከኦዲቱ በኋላ ቅጥር ተፈጽሞ ከሆነ በድህረ-ክትትል ኦዲት የሚጣራ ይሆናል፡፡

46. በመሆኑም የሥነ-ልቦና አማካሪ ባለሙያ የሌለበት ዩኒቨርስቲ መኖሩ፣ ባሉባቸውም ጾታን ያማከሉ አለመሆናቸውና ለአገልግሎቱ ምቹ ያልሆኑ ቢሮዎች መኖራቸው ተማሪዎች የሥነ-ልቦና ችግር ሲገጥማቸው መፍትሔ እንዳያገኙ እንቅፋት ስለሚሆን አሰራሩ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

## የሥነ-ምግባር፣ የሥርዓተ-ጾታና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤቶች ስለመኖራቸውና አገልግሎታቸው የተሟላ ስለመሆኑ፣

47. በየዩኒቨርስቲው የሚገኙ ካምፓሶች የሥነ-ምግባር፣ የሥርዓተ-ጾታና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤቶች ሊኖሯቸው ጽ/ቤቶቹም በሰው ኃይል የተሟሉ ሊሆኑና የተሟላ አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡

48. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ዩኒቨርስቲዎች በአንዳንድ ካምፓሶች ጽ/ቤቶቹ አለመኖራቸውና ባሉበትም የሰው ኃይል እጥረት ያጋጠማቸው ጽ/ቤቶች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

49. ከአራቱም ዩኒቨርስቲ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ እንደተገኘው፣

    በዲላ የሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤት ኃላፊዋ ሥራውን ደርበው የሚሰሩና ሙያቸው ከሥራው ጋር ተያያዥነት የሌለው መሆኑና በሥርዓተ-ጾታ ዙሪያም ስልጠና አለመውሰዳቸው እንዲሁም በጽ/ቤቱ የሰው ኃይል እጥረት መኖሩን፣

    በሀዋሳ የወንዶ ገነት የደንና ተፈጥሮ ሳይንስ ካምፓስ የሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤት ኃላፊው ከሌላ ሥራ በተጨማሪ ሥራውን ደርበው የሚሰሩ መሆናቸውን (ከተከለሰ መረጃ)፣

    በባህር-ዳር የሥነ-ምግባር ጽ/ቤት የሰው ኃይል እጥረት እንዳለና 18 የሰው ኃይል የተፈቀደ ቢሆንም ሥራው እየተሰራ ያለው በሁለት ቋሚ ሠራተኞች ብቻ መሆኑና የሥነ-ምግባር መኮንኑ የጽ/ቤቱን ሥራ ደርበው የሚሰሩ መሆናቸው፣

    በጎንደር የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ባለሙያ አለመኖሩና የሥርዓተ ጾታ ኃላፊዋ ሥራውን ደርበው የሚሰሩ መሆኑን፣

50. እንዲሁም በዲላ ዩኒቨርስቲ ካሉት ሶስት ካምፓሶች ውስጥ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስና የሥርዓተ-ጾታ በዋናው ካምፓስ ብቻ የሥነ-ምግባር ጽ/ቤት በአዲሱ ካምፓስ ብቻ መገኘቱ፣

    በጎንደር ሦስቱም ጽ/ቤቶች በቴዎድሮስ ካምፓስ ብቻ መገኘታቸው፣

    በባህር-ዳር የሥነ-ምግባር ጽ/ቤት በዋናው ካምፓስ፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤት በኢንጅነሪንግ ካምፓስና የሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤት በኤፍ.ቢ. ካምፓስ ብቻ መገኘታቸውና በባህር-ዳር ለሥርዓተ ጾታና ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤቶች፣ ለፕሮክተሮችና ለጥበቃ ሰራተኞች ተዘጋጅቶና ጸድቆ የተሰራጨ የሥራ መዘርዝር (Job description)፣ በዲላና በጎንደር ለሥርዓተ-ጾታ ሰራተኞች የስራ መመሪያ እና በባህር-ዳር የሥርዓተ-ጾታ ፖሊሲ እንደሌለ የየዩኒቨርስቲዎቹ የስራ ክፍል ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

51. በመሆኑም በየዩኒቨርስቲው ካምፓሶች ጽ/ቤቶቹ አለመኖራቸው፣ ባሉበትም የተሟላ የሰው ኃይል፣ የስራ መዘርዝርና የስራ መመሪያ አለመኖሩ ሥራው ተደራሽና የተሟላ እንዳይሆንና ተጠያቂነትን እንዳያሰፍን ስለሚያደርገው አሰራሩ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

## ሴት ተማሪዎችን ለሴትኛ አዳሪነት ተግባር

## አሳልፌው የሚሰጡ ደላሎች ስለመኖራቸው፣

51. የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎችን ለሴትኛ አዳሪነት ተግባር አሳልፌው የሚሰጡ ደላሎች (ተማሪዎችም ሆኑ ሌሎች አካላት) ሲገኙ በተማሪዎች ጠቋሚነት እንዲጋለጡ ለጠቋሚዎቹ ማበረታቻ መስጠትና በደላሎቹም ላይ ህጋዊ እርምጃ ማስወሰድ ይገባል፡፡

52. በኦዲቱ በአራቱም ዩኒቨርስቲዎች በታዩት ካምፓሶች መጠይቅ ሞልተው ከመለሱ ተማሪዎች ሴት ተማሪዎችን ለሴትኛ አዳሪነት ተግባር አሳልፌው የሚሰጡ ደላሎች (ተማሪዎች፣ የግቢው ማህበረሰብና የውጭ አካላት) መኖራቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

53. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት የተከለሰ መረጃ፣

በሀዋሳ፣ በጅማ፣ በመቀሌ፣ በባህር-ዳር፣ በአዳማ፣ በጎንደርና በሐሮማያ ዩኒቨርስቲዎች ሴት ተማሪዎችን ለሴትኛ አዳሪነት ተግባር የሚያግባቡ ደላሎች መኖራቸውን (በከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚገኙ ሴት ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ እንዳይሆኑ የሚያደርጓቸው ምክንያቶች ላይ የተጠና ጥናት ገጽ 55) ያስረዳል፡፡

54. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የየዩኒቨርስቲው የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣

በዲላ አዲሱ ካምፓስ ላይ ችግሩ እንዳለ ደላሎቹም የውጭ አካላት በሞተር ሳይክል ይገቡ እንደነበርና ከፖሊስ ጋር በመቀናጀት የተሠሩ ሥራዎች የነበሩ መሆናቸውን፣ በደላልነት የሚሰሩ ተማሪዎችም የነበሩ መሆኑንና በሥርዓተ ጾታ ጽ/ቤት በኩል ሴት ተማሪዎችን ለብቻ ሰብስበው የግንዛቤ ሥራ ተሰርቶ እንደነበርና (የተማሪዎች ህብረት ኃላፊዎች) ችግሩ እንዳለ መረጃ የሚገኝበት መንገድ(ስልት) ግን እንደሌለ፣ (የዩኒቨርስቲው የአስተዳደር ልማት ም/ፕሬዝዳንት)

በሀዋሳ በውጭም በውስጥም ደላሎች መኖራቸውን፣ የሴት ተማሪዎችን ፎቶ ሆቴል ውስጥ የሚያስቀምጡና የሚያሳዩም መኖራቸውን፣ አካባቢው ለዚህ ተግባር የተጋለጠ መሆኑንና፣ በእድሜ አቻ ያልሆኑ ባለሀብቶችም (ሹገር ዳዲዎች) በዩኒቨርስቲው አካባቢ እንደሚመጡና የባጃጅ ሾፌሮችን፣ ሊስትሮዎችንና ፔንሲዮኖችን በመጠቀም ሴት

ተማሪዎችን የሚያገኙበት ሁኔታ መኖሩን፣ ማታ ማታ ለዚሁ ተግባር ተዘጋጅተው የሚወጡ ሴት ተማሪዎችም እንዳሉ፣ 'አስተኳሽ' የሚባል የተደራጀ ቡድንም በግቢው መኖሩንና የተማሪዎች ካውንስሉ በጉዳዩ ላይ እየሰራበት መሆኑን፣ (የዋናው ግቢ የተማሪዎች መማክርት ኃላፊዎች) የተማሪዎች ፎቶ ሆቴል ይገኛል እንደሚባልና ደላሎችም እንዳሉ እንደሚሰሙ ነገር ግን በተጨባጭ መረጃ እንደሌላቸው፣ (የሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤት ኃላፊ) የሚደልሉ ተማሪዎችን ለይቶ ግንዛቤ መስጠትና ማስተማር እንደሚታሰብና በወሬ ደረጃ በየሆቴሉ ይቀመጣል የተባለውን የተማሪዎች ፎቶ እርግጠኝነት ለማጣራት ጥረት እየተደረገ እንደሆነ፣ (የዩኒቨርስቲው የተማሪዎች አገልግሎት ኃላፊ)

በጎንደር ጉዳዩን በንቃት እንደሚከታተሉ፣ በ2000 ዓ.ም. ላይ የውጭ ሰዎች ሴት ተማሪዎችን ብር እየሰጡ አደራጅተው እንደነበር፣ ከጥበቃ ጀምሮ ሥራ ተሰርቶ አራት ተማሪዎች ከዩኒቨርስቲው እንደተባረሩና በአሁን ሰዓት እንደሌለ፣(የሥርዓተ-ጾታ፣ ጽ/ቤት ኃላፊ) በሌላ መልኩ ደግሞ ተጠቁመው ማጣራት እያደረጉባቸው ያሉ ተማሪዎች እንዳሉና የጥበቃ ፖሊሶችም በር ላይ የሚቆሙ መኪኖችን እንደሚከለክሉ በተለይ በጤና ሳይንስ ካምፓስ ሆስፒታሉ 24 ሰዓት ስለሚሰራ ይህ ጉዳይ በስፋት ጎልቶ እንደሚታይና ለመቆጣጠርም አስቸጋሪ መሆኑንና በካምፓሱ የተመደበው የጥበቃ ፖሊስ እራሱ የደላልነት ሥራ ሲሰራ ተገኝቶ እንደነበር፣ (የጎንደር ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ህብረት መማክርት ኃላፊዎች)

በባህር-ዳር በዚህ ጉዳይ በወሬ ደረጃ መረጃው እንዳለና አጥንቶ ችግሩን ለመፍታት ከግቢው ጥበቃ ፖሊሶች ጋር አብረው እየሰሩ መሆናቸውን፣ (የዩኒቨርስቲው የተማሪዎች አገልግሎት ኃላፊ) በደላሎች ላይ መረጃ እንጂ ማስረጃ ባለመኖሩ መረጃውን ወደ ማስረጃ በመቀየር እርምጃ ለመውሰድ ጥረት እየተደረገ መሆኑን (የዩኒቨርስቲው የጥበቃና ደህንነት ኃላፊ)

ገልጸዋል፡፡

55. ይህ ጉዳይ የሚመለከታቸው የየዩኒቨርስቲው የስራ ኃላፊዎችና የውጪ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት ሆነው መረጃዎችን በማጠናከርና እርምጃ በመውሰድ ሴት ተማሪዎችን መታደግና የየዩኒቨርስቲውን ገጽታ መቀየር እንዳለባቸው ያሳያል፡፡

## ለተማሪዎች በቂ የመዝናኛና

## የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት ስለመኖራቸው፣

56. በየዩኒቨርስቲው የመዝናኛ ማዕከላትንና አገልግሎት መስጫዎችን በማብዛትና በማጠናከር ተማሪዎች ትርፍ ጊዜያቸውን በዩኒቨርስቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዲያሳልፉና ሴት ተማሪዎችም ለጾታዊ ጥቃት እንዳይጋለጡ ሊደረግ ይገባል፡፡

57. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በቦታው በመገኘት ጉብኝት በተደረገባቸው በአራቱም ዩኒቨርስቲዎች፡-

በዲላ ዋናው ካምፓስ በግቢ ውስጥ ያለው አንድ የተማሪዎች ላውንጅ አገልግሎቱ ያልተሟላና ዋጋውም ውጭ ካሉ ካፍቴሪያዎች ጋር ተቀራራቢ መሆኑ፣ አንድ የሸቀጣ ሸቀጥ ሱቅ ያለ ሲሆን የአንዳንድ ሸቀጦች ዋጋ ከግቢው ውጭ ካለው ዋጋ እንኳን የሚበልጥ፣ (አንድ ኪሎ ስኳር ብር ሃያ ስድስት፣ የሞባይል ካርድ በመደበኛ ዋጋው ላይ አንድ ብር ጭማሪ ያለው) አምስት የፑል መጫወቻ፣ አንድ ዲ.ኤስ.ቲ.ቪ፣ መጠለያ የሌላቸው አንድ  የሴትና አንድ የወንድ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አገልግሎት ከመኖራቸው በስተቀር ሌሎች መዝናኛዎችም ሆኑ አገልግሎት መስጫዎች /ፀጉር ቤት፣ ፎቶ ቤት፣ ሱፐር ማርኬት…./ በግቢው አለመኖራቸው፣

በጎንደር በቴዎድሮስና በማራኪ ካምፓስ ከተማሪው ቁጥር አንጻር በቂ መዝናኛና አገልግሎት መስጫ አለመኖሩ፣

በባህር-ዳር በዘንዘልማ ካምፓስ ምንም አይነት መዝናኛዎችና አገልግሎት መስጫዎች አለመኖራቸው፣ በይባብ ካምፓስ  የተሟላ አገልገሎት የማይሰጥ አንድ ላውንጅ፣  አንድ የዲ.ኤስ.ቲቪና ሁለት የቴሌቪዥን አገልግሎት መስጫ ከመኖሩ በስተቀር ሌሎች መዝናኛዎችና አገልግሎት መስጫዎች አለመኖራቸው፣ በዋናውና በኤፍ.ቢ ካምፓስ ከላውንጅ፣ ከሱቅና ከሴቶች ፀጉር ቤት በስተቀር ሌሎች አገልግሎት መስጫዎች አለመኖራቸውና፣ በኢንጅነሪንግ ካምፓስ አንድ ሱቅና ሶስት ላውንጆች፣ ሶስት የፑል መጫወቻዎችና ሶስት የጠረጴዛ ቴኒሶች ቢኖሩም ከተማሪው ቁጥር አንፃር በቂ አለመሆናቸው፣

በሃዋሳ የዋናው፣ በጎንደር የማራኪና የቴዎድሮስ፣በባህር-ዳር የኢንጂነሪንግ፣ የዘንዘልማና የይባብ ካምፓሶች ለሴቶች ብቻ ተብሎ የተከፈተ የማንበቢያ ክፍል የሌላቸው መሆኑና በዲላም በዋናው ካምፓስ በዶርማቸው አካባቢ ያለው አንድ የሴት ተማሪዎች ማንበቢያ

ክፍል በግምት 20 ተማሪ ብቻ ማስተናገድ የሚችል ከመሆኑም በላይ በኦዲቱ ወቅት አገልግሎት የማይሰጥና ሙሉ ለሙሉ መጽሐፍ የተቀመጠበት መሆኑና፣ በባህር-ዳር በዋናው ግቢ ያለውም አንድ የሴቶች ማንበቢያ ክፍል በግምት 30 ተማሪ ብቻ ማስተናገድ የሚችል መሆኑ ታይቷል፡፡

58. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች በየዩኒቨርስቲው በቂ የመዝናኛ ማዕከላትና አገልግሎት መስጫዎች የሌሉባቸው የየዩኒቨርስቲ ካምፓሶች መኖራቸው ታውቋል፡፡ የተከለሰው መረጃ በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡

59. በተጨማሪም የየስራ ክፍሉ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፡-

በዲላ መሠረታዊ የሚባሉ የመዝናኛ ማዕከላት፣ ክበባትና ካፍቴሪያዎች አለመኖራቸውንና ተማሪዎቹ በፈተና ሰዓት ቡና መጠጣት ቢፈልጉ እንኳን ከግቢ ወጥተው እንደሚጠቀሙ፣ የወንድና የሴት ፀጉር ቤት በመዘጋቱና ግቢ ውስጥ ያለው ባንክ ቤት በሳምንት አንድ ቀን ብቻ የሚከፈት በመሆኑ አገልግሎቱን ለማግኘት ከተማ ሄደው በዛው ወደ አልተፈለገ ቦታ እንደሚሄዱ፣ (የፕሮክተር ኃላፊዎች)

በሃዋሳ ለሴት ተማሪዎች የማንበቢያ ክፍል ወንበር ማሟላት ብቻ እንደቀረውና በቅርብ ስራ እንደሚጀምር፣ መጽሐፍት ቤትም የመፅሐፍ ቁጥር አናሳ በመሆኑ እንዲሟላ ጥረት እየተደረገ እንዳለ፣ (የሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤት ኃላፊ)

በባህር-ዳር የመዝናኛ ቦታ ሥራው በቂ እንዳልሆነ ከእርዳታ ሰጪዎች ጋር እየሰሩ መሆናቸው ስራውን እንዳዘገየውና በዩኒቨርስቲው በራሱ መሠራት እንዳለበት (የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤት ኃላፊ) ጉዳዩ ያልተሰራበትና ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ መሆኑን (የባህር-ዳር ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች አገልግሎት ኃላፊ)

ገልጸዋል፡፡

60. በአንጻሩ የማንበቢያ ክፍልን በተመለከተ ሴቶችና ወንዶች አብረው ማጥናት አለባቸው የሚል የግል አቋም እንዳላቸውና ለዚህም ምክንያቱ ሴት ተማሪዎች ከዩኒቨርስቲ ወጥተው በሥራ አለም ከወንዱ ጋር ስለሚሆኑ የሴቶችን አስተሳሰብ መገንባት እንዳለባቸው የባህር-ዳር ዩኒቨርስቲ ኃሬዘዳንት ገልጸዋል፡፡

61. ሆኖም ተማሪዎች የተለያዩ መዝናኛዎችንና አገልግሎቶችን ፍለጋ ወደውጪ በመውጣት ለሥነ-ምግባር ብልሹነት እንዳይዳረጉ እንዲሁም ሴት ተማሪዎች ለብቻ ማግኘት የሚገባቸውን አገልግሎት ሳያገኙ ቀርተው ለጾታዊ ትንኮሳ እንዳይጋለጡ በየዩኒቨርስቲው

በቂና የተሟላ የመዝናኛ አገልግሎት መስጫ አለመኖሩ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

## የቅንጅት ሥራና የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ስለመኖሩ፣

62. የሥርዓተ-ጾታ፣ የሥነ-ምግባር፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤቶች፣ አማካሪ ባለሙያዎች፣ ኘሮክተሮችና የጥበቃ ሰራተኞች በቅንጅት የሚሰሩበት መድረክ ሊኖራቸው፣ የየዩኒቨርስቲው ሥራ አመራሮችም የሥራ አፈጻጸማቸውን በመገምገም በተገኙ ክፍተቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል::

63. በባህር-ዳር ዩኒቨርስቲ በ2005 ዓ.ም. በጋራ ለመሥራት የተያዘ ዕቅድ መኖሩን በኦዲቱ ወቅት ከቀረበ የዕቅድ ሪፖርት ለመረዳት የተቻለና ጅምር ስራው የሚበረታታ ሲሆን በቀሩት ሦስት ዩኒቨርስቲዎች ግን በቅንጅት የመስራት ልምድ እንደሌለና ሥራ አመራሩም የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶችን በመገምገም አፋጣኝ እርምጃ የማይወስድባቸው ክፍተቶች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

64. ለየዩኒቨርስቲው የሥራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ እንደተቻለው፣

 በዲላ፣ በሀዋሳና በባህር-ዳር የሥርዓተ-ጾታና የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ጽ/ቤቶች አብረው እንደሚሰሩ ከሌሎቹ ጋር ግን አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲኖሩ ካልሆነ በስተቀር በቋሚነት አብረው የሚሰሩበት ሁኔታ እንደሌለ፣ (የየዩኒቨርስቲው የሥርዓተ-ጾታ ኃላፊዎች)

 በሀዋሳ በቅንጅት እንዳልተሰራና ተጠያቂነትን ለማጠናከር አብረው ለመስራት በዕቅድ እንደተያዘ፣ (የተማሪዎች አገልግሎት ኃላፊ)

 በባህር-ዳር በተናጠል እንጂ ከሌሎች ጋር በጋራ የሚሠሩበት ሁኔታ እስከአሁን እንዳልነበረ፣(የሥነ-ምግባር ጽ/ቤት ኃላፊ)

 ገልጸዋል፡፡

65. እንዲሁም የሥራ አመራር ግምገማን አስመልክቶ፣

 በዲላ ከኘላንና ኘሮግራም ግብረ መልስ በተወሰነ መልኩ እንዳለ፣(የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤት ኃላፊ)

 በባህር-ዳር በየሦስት ወሩ ለኘሬዝዳንት ጽ/ቤት ሪፖርት እንደሚያቀርቡ ነገር ግን ተገምግሞ ግብረ መልስ እንደማያገኙና ከአመራሩ ጋር ቋሚ ስብሰባ እንደሌላቸው፣ ተማሪዎች ከመግባታቸው በፊት ችግሮች እንዲስተካከሉ ለሚመለከታቸው አካላት ሳምንታዊ ሪፖርት ቢያቀርቡም ችግሮቹ እንደማይስተካከሉና በሚቀጥለው ሳምንት ሪፖርትም በፊት የቀረቡት

ችግሮች በድጋሜ እንደሚነሱ፣ (የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤትና የፕሮክተር ኃላፊዎች በተከታታይ)
ገልጸዋል፡፡

66. በተጨማሪም በሀዋሳ፣ በባህር-ዳርና በጎንደር የተማሪውን ማደሪያ ክፍል(ዶርም) ጽዳት የማይከታተሉ፣ ከተማሪው ጋር ጓደኝነት በመመስረት ሲጋራ በሚያጨሱና ጫት በሚቅሙ ተማሪዎች ላይ እርምጃ የማይወስዱ፣ ተማሪዎች ከግቢ ሲባረሩ ከዶርም የማያስወጡ፣ እራሳቸው የሚቅሙ፣ የሚያጨሱና ሰክረው የሚገቡ፣ የተማሪ ንብረት የሚሰርቁ፣ በሥራ ሰዓታቸው በሥራ ገበታቸው ላይ የማይገኙ ፕሮክተሮች መኖራቸውን፣ በተማሪዎች ተሞልቶ ከተመለሰ መጠይቅ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ በባህር-ዳር የሰው ኃይል እጥረት ትልቁ ችግር እንደነበረና ሥርዓት የጐደላቸው ፕሮክተሮች እንዳሉ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የተማሪው ህብረት እንዲከታተል እያደረጉና እየመከሩ እንደሆነ የተማሪዎች አገልግሎት ኃላፊ ገልጸዋል፡፡

67. ስለጉዳዩ የየዩኒቨርስቲው ፕሬዘዳንቶች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣
በዲላ በእቅድ፣ በእቅድ አፈፃፀምና በግምገማ ላይ የስራ ክፍሎቹ እንደሚገናኙ፣
በሀዋሳ የሥራ ክፍሎቹ በፕሬዘዳንት ጽ/ቤት ሥር ያሉ ሲሆኑ ከመምህርነት ሥራቸው በተጨማሪ የሚሰራ በመሆኑ ችግሩ እንዳለ ነገር ግን በየሶስት ወሩ ሪፖርት እንደሚያቀርቡና የግምገማ ሥርዓትና መድረኮችም እንደሚዘጋጁ፣
በጎንደር በየወሩና በየሦስት ወሩ ሪፖርት እንደሚቀርብና በየወሩ ግምገማ እንደሚደረግ የግዴታም አብራችሁ ሥሩ የሚልም መመሪያ እንደሌለ ነገር ግን በቅንጅት የመሠራቱ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንደሄደና
በባህር-ዳር ክፍሎቹ በ2005 ዓ.ም. በጋራ አቅደው ሊሰሩ እንዳሰቡ በፕሮክተሮች ላይም አሉ የተባሉት ችግሮች ልክ እንደሆኑና እስከዛሬ በዩኒቨርስቲው ሥራ እንዳልተሰራ በሚቀጥሉት ጊዜያት ግን እንደሚያስተካክሉ ገልጸዋል፡፡

68. ሆኖም የሥነ-ምግባር፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ የሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤቶች፣ አማካሪ ባለሙያዎች፣ ፕሮክተሮችና የጥበቃ ሰራተኞች በጋራ አለመስራታቸውና የሥራ ክፍሎቹም በስራ አፈጻጸም የሚያጋጥሟቸው ችግሮች በበላይ አካል ተገምግሞ በወቅቱ ምላሽ አለማግኘቱ ለተማሪዎች የሥነ-ምግባር ብልሹነት መንገድ የሚከፍት ሊሆን ስለሚችል አሰራሩ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

## የተማሪዎች መኖሪያ/ዶርም/ና የዩኒቨርስቲዎቹን ቅጥር ግቢ ሁኔታ በተመለከተ፣

69. የሴትና የወንድ ተማሪዎች መኖሪያ/ዶርም/ የተራራቀ ወይም በአጥር የተከለለ ወይም ጥበቃ የሚደረግለት ሊሆን እንዲሁም ተማሪዎቹ ለሥነ-ምግባር ችግር እንዳይጋለጡ የዩኒቨርስቲዎቹ ቅጥር ግቢ አጥር ሊኖረውና በምሽት ጨለማ የሆኑ ሁሉም ቦታዎች የኤሌክትሪክ ብርሃን ሊኖራቸው ይገባል፡፡

70. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በቦታው በመገኘት ጉብኝት በተደረገባቸው በአራቱም ዩኒቨርስቲዎች፡-

    በዲላ የዋናውና በጎንደር የማራኪና የቴዎድሮስ ካምፓሶች የሴትና የወንድ ተማሪዎች መኖሪያ(ዶርም) የተቀራረበ፣ (በግምት አስር ሜትር ርቀት ያለው) በአጥር ያልተከለለና ጥበቃም የሌለባቸው (የማይደረግ) መሆኑና በባህር-ዳር የዘንዘልማ ካምፓስ የሴቶች ዶርም ላይ የተመደቡት ፕሮክተሮች ወንዶች መሆናቸው፣

    በዲላ ዋናውና አዲሱ ካምፓስ፣ በሀዋሳ ዋናው ካምፓስ፣ በጎንደር ማራኪ፣ ቴዎድሮስና አጼ-ፋሲል ካምፓስ፣ በባህር-ዳር ዋናውና ኤፍ. ቢ. ካምፓስ ከፊት ለፊት በስተቀር ዙሪያውን አጥር የሌላቸው መሆኑ፣ በጎንደር ብሪጅ ኦፍ ሆፕ የሚባል ድርጅት በቴዎድሮስ እና በአጼ-ፋሲል ካምፓስ መካከል በመገኘቱና የግለሰቦችም መኖሪያ ቤቶች በመኖራቸው ምክንያት ከተቋሙ ማህበረሰብ ውጪ ያሉ ሌሎች አካላት ግቢውን እያቋረጡ ማለፋቸውንና በሁሉም ዩኒቨርስቲዎች በታዩ ካምፓሶች ግቢ ውስጥ በምሽት መብራት የሌላቸው ጨለማ ቦታዎች መኖራቸውን ለማየት ተችሏል፡፡



ፎቶ 2፣ የጎንደር ማራኪ ካምፓስ የተቀራረበ፣ አጥር የሌለውና ጥበቃ የማይደረግለት የወንድና የሴት ዶርም

የሴት ዶርም

የወንድ ዶርም

71. እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች፡-

በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ የሴቶች ዶርም አጥር ባለመኖሩ የተነሳ ወንድ ተማሪዎች የሴቶች ዶርም በመግባት ጾታዊ ትንኮሳ እንደሚያደርሱና ዲላ ዩኒቨርስቲ አዲስ በመሆኑ ግቢው ጭራሽ አጥር ባለመኖሩ ለሴት ተማሪዎች እንደልባቸው ለመንቀሳቀስ ስጋት ላይ መጣሉን፣ (የወላይታ ሶዶና የዲላ ዩኒቨርስቲ በትምህርት ሚኒስቴር የሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤት የክትትል ሪፖርት)

በባህር-ዳር በፔዳ ካምፓስ በግቢ ውስጥ በምሽት ጨለማ የሆኑ ቦታዎች መኖራቸውን፣ (የባህር-ዳር ዩኒቨርስቲ የ2003 የሥርዓተ-ጾታ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ገጽ 6) እንዲሁም በሀዋሳ ግቢው አጥር የሌለው በመሆኑ ያልተፈለጉ ግለሰቦች እስከ መኝታና ቴሌቪዥን ክፍል ድረስ የመግባት ችግር መኖሩን፣ (የተማሪዎች ጉዳይ ጽ/ቤት የ2004 የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት) መረዳት ተችሏል፡፡

72. በተጨማሪም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጥያቄው ቀርቦ፡-

በባህር-ዳር የዋናው ግቢ ጫካ በመሆኑና መብራት በሚገባ ስለሌለው ለጥበቃ ብዙ የሰው ኃይል የሚያስፈልገው መሆኑንና ጭለማውን በመጠቀም ተማሪዎች ወሲብ

እንደሚፈጽሙ፣ የውጭ አካላትም ወደ ውስጥ እየገቡ የተለያዩ ተግባራትን እንዲፈጽሙ በር እንደከፈተ፣(የፕሮክተር ኃላፊዎች)

በሀዋሳ የዋናው ግቢ በምሽት የሚጨልሙ ቦታዎች በመኖራቸው ተማሪዎች በጨለማ ለረጅም ሰዓት የሚቀመጡበት ጊዜ መኖሩንና ለወሲብ ተግባርም እንደተጋለጡ ለዚህም የመብራት ብርሀን በጨለማ ቦታ መለቀቅ እንዳለበት (የሥነ-ምግባር ጽ/ቤት ኃላፊ) ገልጸዋል፡፡

73. እንደዚሁም የየዩኒቨርስቲው ኃላፊዎች በሰጡት መልስ፡-

በዲላ የነበሩና አገልግሎት ያቋረጡ መብራቶችን ቶሎ ቶሎ የመጠገን ችግር እንዳለ፣ በግንባታ ሂደት ላይ ያሉትም ወደፊት እንደሚሰሩና የማስተካከያ ሥራ ለመሥራት ጥረት እንደሚደረግ፣

በሀዋሳ ለአጥር ተብሎ የሚመደብ በጀት እንደሌለ ሆኖም ወደ 250 ሄክታር የሚደርስ ስፋት ያለውን የዋናውን ግቢ አጥር ለማሳጠር ለኮንትራክተር እንደተሰጠ፣ መብራት አለመኖሩም ከስፋቱ ጋር የሚገናኝና ግቢው ውበት እንዲኖረው ጭምር አንድ ትልቅ ፕሮጀክት እየተሰራ ያለበት ሁኔታ እንዳለ፣

በጎንደር አጥር ያለመኖሩና የሚጨልሙ ቦታዎች መኖራቸው እውነት መሆኑን፣ አጥር ባለመኖሩም ለጥበቃ ከባድና የጥበቃ ወጪንም እንደጨመረ፣ በቴዎድሮስ እና በአጼ-ፋሲል ካምፓስ መሀል ብሪጅ ኦፍ ሆፕ የሚባል ድርጅት መኖሩም ችግር እንደፈጠረ ሆኖም ወደ መፍትሔ ለመምጣት እየሰሩ መሆኑንና መብራቶችም እንዲስተካከሉ እንደሚያደርጉ፣ በባህር-ዳር የአጥር ሥራ እየሔዱበት መሆኑንና በዘንዘልማ ካምፓስ በሴቶች ዶርም የሚገኙት ፕሮክተሮች ወንዶች ከሆኑ ልክ እንዳይደለና ጉዳዩን እንደሚያጣሩ፣ በዲላ የአስተዳደር ልማት ም/ፕሬዝዳንት እና የየዩኒቨርስቲው ፕሬዘዳንቶች ገልጸዋል፡፡

74. በመሆኑም የሴትና የወንድ ተማሪዎች መኖሪያ/ዶርም/ የተቀራረበ ወይም በአጥር የተከለለ ወይም ጥበቃ የማይደረግበት መሆኑና የመሠረተ ልማት አገልግሎት መጓደሉ ተማሪውን ለሥነ-ምግባር ችግር እንዲጋለጥ ሊያደርገው ይችላል፡፡

**ተማሪዎች ሊደርስባቸው ከሚችሉ አካባቢያዊ ተፅዕኖ ለመከላከል ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የቅንጅት ስራ በተመለከተ፣**

75. ዩኒቨርስቲዎች በአካባቢያቸው የጫት፣ የሺሻ፣ የመጠጥ፣ የጭፈራ እና የመሳሰሉት ቤቶች እንዳይኖሩ ለማድረግ ከከተማ መስተዳድሮች፣ ከፖሊስ አካላት፣ ከማዘጋጃ ቤቶችና ክፍለ ከተሞች ጋር በቅንጅት የሚሰሩበት መድረክ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

76. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ዩኒቨርስቲዎች፣
በዲላ ዩኒቨርሲቲ በአዲሱ ካምፓስ በሀዋሳ ዩንቨርሲቲ ዋናውና የጤና ሳይንስ ካምፓስ፣ በጎንደር ቴዎድሮስና ማራኪ ካምፓስ በባህር-ዳር በዋናው ካምፓስ አካባቢ የጫት፣ የሺሻ፣ የመጠጥ ቤቶችና በባህር-ዳር በዘንዘልማና በሀዋሳ በዋናው ካምፓሶች አካባቢ የጫት እርሻ መኖራቸው ታውቋል፡፡ በተጨማሪም በዲላ ዩኒቨርሲቲ በአዲሱ ካምፓስ አካባቢ የሚገኙትን የጫት፣ የሺሻ እና የመጠጥ ቤቶች ለማስወገድ በተቋሙና በባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የተሰሩ ስራዎች እንደነበሩ መረጃ ቢገኝም (በኦዲቱ ወቅት እነዚሁ ቤቶች በተቋሙ አካባቢ እንደገና ተስፋፍተው መገኘታቸው) በሌሎቹ ዩኒቨርስቲዎች ግን ከባለድርሻ አካላት ጋር የቅንጅት ስራ ስለመሰራቱ መረጃ አልተገኘም፡፡

77. እንዲሁም ፖሊስና እርምጃው መስከረም 16 ቀን 2005 ዓ.ም. ባወጣው እትሙ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ይፋ ባደረገው ጥናት የጫትና ሺሻ ቤቶች ሆን ብለው የሚከፈቱትና የሚስፋፉት ት/ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች ባሉባቸው አካባቢዎች እንደሆነና ይህ በመሆኑም በተማሪዎች ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን ይገልጻል፡፡

78. የሚመለከታቸውም የሥራ ኃላፊዎች በጉዳዩ ላይ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፡-
በዲላ ከላይ ምግብ ቤት ተብሎ ተለጥፎ በመጋረጃ ተሸፍኖ የሚቃምባቸው ቤቶች እንዳሉ፣ (የተማሪዎች መማክርት) ዕፅ ነጋዴና ተጠቃሚ ተማሪዎች መኖራቸውን፣ (የኘሮክተር ኃላፊዎች) የመሬት ፍቃድ ሲሰጥ ለንግድ ተብለው የተሰጡት በጣም ውስን እንደሆኑና ለመኖሪያ ቤት መስሪያ የወሰዱትን ቦታ በህገ-ወጥ መንገድ እንደሚነግዱበትና በግለሰቦቹም ላይ እርምጃ ለመውሰድ ቦታና ፍቃድ የሚሰጠው አካል እና ፖሊስ ቅንጅታዊ አሰራር የጎደላቸው መሆኑንና ተማሪዎችን በሚመለከት ጉዳይ ላይ ለመነጋገር በዩኒቨርስቲው የተፈጠረ መድረክ እንደሌለ፣ (የከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ) በ2004 ዓ.ም. በዩኒቨርስቲ አካባቢ ያሉ ሺሻ ቤት ባለቤቶች ላይ ክስ እንደመሠረቱ አሁንም በዙሪያው ያሉትን ጫትና

ሺሻ ቤቶች ለማፅዳት በዕቅድ እንደያዙ፣ (የከተማ አስተዳደር ፓሊስ መምሪያ ኃላፊ) ገልጸዋል፡፡

በሀዋሳ ጫት መሸጫ፣ ሺሻ ማጨሻና መጠጥ ቤቶች እንዲሁም የጫት እርሻ በአካባቢው መኖራቸውንና የቁጥጥር ሥርዓቱም የላላ መሆኑን፣ (የሥርዓት-ጾታና የግቢ ፖሊስ ኃላፊዎች) በ2005 ዓ.ም. 101 ተማሪዎች (96 ከዋናው ግቢና 5 ከግብርና ካምፓስ) በሺሻ ቤት እንደተያዙና ከነዚህ ውስጥ 13ቱ አዲስ ተማሪዎች መሆናቸውን፣ በ2004 ዓ.ም. ሺሻ ሲጠቀሙ ተይዘው ተመክረው የተመለሱ ተማሪዎች እንደነበሩ፣ ከሺሻ ቤት ጋር በተያያዘ ህጉ ላይ ክፍተት እንዳለና ነገር ግን ፍቃድ የሌላቸው እንዲዘጉ እንደተደረገ፣ በዩኒቨርስቲው በኘሮግራም ተይዞ በተማሪዎች ሥነ-ምግባር ላይ እንዲሰራ ያልተደረገና ተቀናጅቶ የመስራት ሥራው ገና እንደሚቀረው፣ (የፖሊስ መምሪያው ኃላፊ) በአካባቢው ያሉት ጫት ቤቶችና መጠጥ ቤቶች ቀደም ብሎ ፍቃድ የተሰጣቸው መሆኑንና ሆኖም ከአካባቢው የማራቅ ሥራ እንደተሰራ ነገር ግን ተመልሰው የሚመጡበት ሁኔታ እንዳለ ነገር ግን አዲስ በሚሰጡት ፍቃድ ላይ ጥንቃቄ እየተደረገ መሆኑን፤ ከዩኒቨርስቲውም ጋር የተማሪዎች ውይይት ሲኖር ከማሳተፋቸው ውጭ በችግሮቹ ዙሪያ በከተማ አስተዳደር ደረጃ እንዳልተሳተፉ (የሀዋሳ ከተማ ከንቲባ) ገልጸዋል፡፡

በጎንደር ዋናው ግቢ(በማራኪና በቴድሮስ ካምፓስ) አካባቢ በግምት ከግቢው 50 ሜትር ርቀት ባለው ቦታ ላይ ጫት መሸጫ ቤት መኖሩ፣ በዓፄ ፋሲል ካምፓስ በስተጀርባ የሚገኙ መኖሪያ ቤቶች ተማሪን እንደ ዋና ደንበኛ በመቁጠር የሚያስጨፍሩ፣ የሚያስቅሙና ሺሻ የሚያስጨሱ እንዳሉ፣ (የግቢው ፓሊስ ኃላፊ) ጫት በዝውውር ሲገኝና መቃሚያ ቦታ ስለማይፈቀድ የሚያስቅሙ ከተገኙ እርምጃ እንደሚወሰድ፣ ሀሺሽም ህገወጥ በመሆኑ ክትትል እንደሚደረግ ነገር ግን ጫት መቃሚያና ጭፈራ ቤቶች ህጋዊነት ስላላቸው ለማዘጋት እንደማይቻል፣ (የከተማው ፖሊስ መምሪያ ኃላፊ) ከዩኒቨርስቲው በታች ባለው ሰፈር የሚኖሩ ሰዎች የዩኒቨርስቲውን የውስጥ መንገድ ስለሚጠቀሙ የራሳቸውን መንገድ ለማውጣት እንደታሰበ ጫት የሚያስቅሙትም አስተዳደሩ ለመኖሪያ ቤት እንጂ ለሌላ አገልግሎት እንዳልሰጣቸውና ትልቁ ችግር ዩኒቨርስቲውና ከተማ አስተዳደሩ በጋራ ያልሰሩት ሥራ እንደሆነ (የከተማው አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት ኃላፊ) ገልጸዋል፡፡

በባህር-ዳር በዋናው ካምፓስ አካባቢ ያሉ የኮንቴነር ቤቶች ለጫት፣ ለሺሻና ለመጠጥ ስራ እንደዋሉ፣ እንዲሁም በይባብ ካምፓስ ጫት መቃሚያ እና ሺሻ ማጨሻ ቤቶች፣

በዘንዘልማ ካምፓስ አካባቢ የጫት ተክል መኖራቸውን፣ (የተማሪዎች መማክርት ኃላፊዎች) በየቦታው ሲቅሙ ከሚገኙት ሰዎች መካከል 90 በመቶ ያህሉ  የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች መሆናቸውን፣ ለጫት ንግድና ለጭፈራ ቤት  ህጋዊ ፍቃድ ያላቸው ነጋዴዎች በመኖራቸው ሥራውን የማስቆም ህጋዊነት እንደሌለና ህጋዊ ከለላ ቢኖር ግን እነሱም ተጨምረው እንደሚሰሩ (የከተማው ፖሊስ መምሪያ ኃላፊ) ገልጸዋል፡፡

79. በተጨማሪም በዩኒቨርስቲ አካባቢ ጭፈራ ቤቶች ባይኖሩም በሀዋሳ የ2005 ተማሪዎች ቅበላ ጥቅምት 10 ቀን 2005 ዓ.ም. የእንኳን ደህና መጣችሁ ፓርቲ አዘጋጅተው ከዩኒቨርስቲው ፊት ለፊት ፖስተር ለጥፈውና በራሪ ወረቀት በትነው እንደነበርና ሆኖም ስራቸውን ለማስቆም ጥረት እንደተደረገ፣(የተማሪዎች አገልገሎት ኃላፊ) በጎንደር በማራኪ ካምፓስ አርብ ጥቅምት 30 ቀን 2005 ዓ.ም. ተማሪዎችን ለጭፈራ የሚጋብዝ ፖስተር በግቢ ውስጥ ተለጥፎ መገኘቱን (የስነ-ልቦና አማካሪ ባለሙያ) ከቃለ-መጠይቅና በመረጃነት ከቀረቡት ማስታወቂያዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡






**ፎቶ 2፣ በሀዋሳ የተማሪዎች ቅበላ ቀን (ጥቅምት10/2005) አዲስ የሚገቡ ተማሪዎችን በጭፈራ ቤት ለመቀበል በዩኒቨርስቲው ፊት ለፊት ተሰቅሎ የነበረ የሁለት ጭፈራ ቤቶች ማስታወቂያ**




**ፎቶ 3፣ በሀዋሳ የቅበላ ቀን /ጥቅምት 10/2005/ አዲስ ለሚገቡ ተማሪዎች ከጭፈራ ቤት የተበተነ በራሪ ወረቀት**




**ፎቶ 4፣ በጎንደር ዩኒቨርስቲ የተማሪ ቅበላ ቀን በማራኪ ካምፓስ የተለጠፈ የጭፈራ ቤት ማስታወቂያ**

80. ስለጉዳዩ የየዩኒቨርስቲው ኃሬዝዳንቶች ተጠይቀው ከሰጡት መልስ ለመረዳት እንደተቻለው፣ በዲላ ችግሩ እንዳለና በቀጣይነት ከማህበረሰቡ ጋር መሥራትና በተማሪውም ላይ

የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት በትኩረት መሰራት እንዳለበት፣  በጎንደር አካባቢው ያሉትን ቤቶች ለማፅዳት  ከዩኒቨርስቲው ዋናው በር ፊት ለፊት ያለውን ቦታ በተሻለ መልኩ ለመለወጥ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ጋር ግን በቂ ትብብር እንደሌለ
ገልጸዋል፡፡

81. በመሆኑም ሁሉም ዩኒቨርስቲዎች በየጊዜው የባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ በየዩኒቨርስቲ አካባቢዎች ያሉት ንግድ ቤቶች  ተማሪውን ለሱስና ለሥነ-ምግባር ጉድለት የማያጋልጡ መሆናቸውን እንዲሁም ተማሪዎች በከተማ ውስጥ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ጤናማ መሆኑን ማረጋገጥ ቢችሉ መልካም ነው፡፡

## በየዩኒቨርስቲዎቹ መግቢያ በርና በየአገልግሎት መስጫ (ቢሮዎች) አካባቢ አቅጣጫ ጠቋሚ ሰሌዳ  መኖሩንና፣ ተማሪው_አገልግሎት በሚያገኝበት ቦታ የሀሳብ መስጫ ሳጥን መቀመጡን በተመለከተ፣

82. በየዩኒቨርስቲዎቹ መግቢያ በርና በየአገልግሎት መስጫ (ቢሮዎች) አካባቢ አቅጣጫ ጠቋሚ ሰሌዳ ሊኖርና ሀሳብ መስጫ ሳጥኖችም/ Suggestion Boxes/ በዩኒቨርስቲው ቅጥር ግቢ በተለያየ ስፍራ እንዲኖር ሊደረግ፣ ተማሪዎችም ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ሊበረታቱ፣ ለሚያነሱት ተገቢ ጥያቄና ቅሬታም የሚመለከተው አካል ወቅታዊ መፍትሄዎች ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

83. ይሁንና በኦዲቱ ወቅት በዲላ፣ በሀዋሳ፣ በጎንደርና በባህር-ዳር ዩኒቨርስቲዎች በናሙና በታዩ ካምፓሶች በተደረገ ጉብኝት በመግቢያ በርና በየአገልግሎት መስጫ (ቢሮዎች) አካባቢ አቅጣጫ ጠቋሚ ሰሌዳ አለመኖሩንና ተማሪው አገልግሎት በሚያገኝበት ቦታ ሁሉ የሀሳብ መስጫ ሳጥን አለመቀመጡን ለማወቅ ተችሏል፡፡

84. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው
በዲላ በ2005 ዓ.ም. 10 የሀሳብ መስጫ ሳጥን እንዲሰራ ጠይቀው ትግበራ ላይ እንደሆኑና አቅጣጫ ጠቋሚ የሚለውም ትክክል እንደሆነ፣ (የሥነ-ምግባር ጽ/ቤት አስተባባሪ)
በሀዋሳ የሀሳብ መስጫ ሳጥን በዋናው ግቢ 8 በሌሎች ደግሞ አራት አራት ያሉ መሆናቸውን አቅጣጫ ጠቋሚውም ቢሆን ትክክለኛ አስተያየት እንደሆነና አሁን ዘመናዊ በሆነ መልኩ በየቦታው አቅጣጫ ጠቋሚ ሊሰራ እንደታሰበ፣ (የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ፕሬዘዳንት)

በጎንደር ተማሪው በተማሪ ህብረት የተደራጀ በመሆኑ ቅሬታ ካለው በህብረቱ በኩል ማቅረብ እንደሚችል፣ አቅጣጫ ጠቋሚውም እየታሰበበት እንዳለ፣ (ጎንደር ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት)

በባህር-ዳር የሀሳብ መስጫ ሳጥኖቹን በተመለከተ ለወደፊት ሀሳቡን የሚቀበሉትና አቅጣጫ ጠቋሚ የሚለውም ላይ ስህተታቸው እንደሆነ ማስተካከያም እንደሚደረግ፣ (የባህር-ዳር ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች አገልግሎት ኃላፊ)

ገልጸዋል፡፡

85. አቅጣጫ ጠቋሚና ሀሳብ መስጫ ሳጥኖች/ Suggestion Boxes/ በየዩኒቨርስቲው ቅጥር ግቢና በየአገልግሎት መስጫዎች አካባቢ እንዲኖር አለመደረጉ ተማሪዎችም ሆኑ ሌሎች የተቋሙ ተገልጋዮች ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ስለሚያደርጋቸው ትኩረት ተሰጥቶ አለመሰራቱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

# ክፍል ሦስት

# የመደምደሚያ ሀሳቦች

1. የማስፈፀሚያ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ስለመኖራቸው፣ ለሚመለከታቸው አካላት ስለመዳረሳቸው፣ ስለመተግበራቸውና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ስለመሰራታቸው ለማጣራት ኦዲት ተደርጎ በዝርዝር የኦዲት ግኝቶች ላይ የተመለከቱት ጉልህ የሆኑ የአሠራር እና የአፈፃፀም ግድፈቶች ታይተዋል፡፡ እነርሱም፡-
   - ተዘጋጅቶ ለመምህራን የተሰራጨ የሥነ-ምግባር ደንብና የዲሲፕሊን መመሪያ አለመኖሩ፣
   - የተማሪዎች የሥነ-ምግባር ደንብና መመሪያ ቢኖርም ግንዛቤውን ያላገኙ አንዳንድ ተማሪዎች መኖራቸው፣
   - የኢኮኖሚ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ተጠቃሚ ለማድረግ የተዘጋጀ የመመልመያ መስፈርት አለመኖሩ፣
   - በማጠናከሪያ ትምህርት (ቲቶሪያል ክላስ) አሠጣጥ ላይ የወጣ መመሪያ አለመኖሩ፣
   - የሥራ መዘርዝር (Job description) ያልደረሳቸው (የሌላቸው) በናሙና በታዩ ዩኒቨርስቲዎች የሚገኙ የሥርዓተ-ጾታ፣የሥነ-ምግባርና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤት ሰራተኞችና ፕሮክተሮች መኖራቸው፣
2. የተለያዩ የሥነ-ምግባር ግድፈቶች የተገኙባቸው አንዳንድ መምህራን ተማሪዎችና የዶርም ተቆጣጣሪዎች (ፕሮክተሮች) መኖራቸው፣
3. የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን ለሴትኛ አዳሪነት ተግባር አሳልፈው የሚሰጡ ደላሎች(ተማሪዎች፣የተቋሙ ማህበረሰብና የውጪ አካላት) መኖራቸው፣
4. የሥነ-ልቦና አማካሪ ባለሙያዎች የሌሉባቸው ካምፓሶች መኖራቸውና ባሉባቸውም አማካሪዎቹ ጾታን ያማከሉ አለመሆናቸው፣
5. በሁሉም ዩኒቨርስቲ ያለው የማጠናከሪያ ትምህርት አሰጣጥ ወጥነት የሌለው መሆኑ፣
6. በቀጥታ ከተማሪው ሥነ-ምግባር ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያለውን ስራ የሚሰሩ በየዩኒቨርስቲው የሚገኙ የሥርዓተ-ጾታ፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስና የሥነ-ምግባር ጽ/ቤቶች፣ የዶርም ተቆጣጣሪዎችና የጥበቃ ሰራተኞች በቅንጅት የሚሰሩበት መድረክ የሌላቸው ዩኒቨርስቲዎች መኖራቸው፣
7. የሥርዓተ-ጾታ፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስና የሥነ-ምግባር ጽ/ቤቶች የሌሏቸው ካምፓሶች መኖራቸው፣

8. በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ባጋጠመ የአፈጻጸም ችግር ላይ የአመራር አካላት አፋጣኝ እርምጃ የመውሰድ ችግር መኖሩ፣

9. የተቀራረበ የሴትና የወንድ ተማሪዎች መኖሪያ /ዶርም/ ባለባቸው የየዩኒቨርስቲው ካምፓሶች መኖሪያቸው በአጥር ያልተከለለ፣ ወይም ጥበቃ የማይደረግበት መሆኑ፣

10. ለሴት ተማሪዎች ለብቻ የተዘጋጀ የማንበቢያና የቴሌቪዥን /TV room/ አገልግሎት መስጫ ክፍል የሌላቸው ዩኒቨርስቲዎች መኖራቸው፣

11. በቂ የመዝናኛ ማዕከላትና አገልግሎቶች መስጫዎች የሌሏቸው ዩኒቨርስቲዎች መኖራቸው፣

12. ተማሪዎችን ለሥነ-ምግባር ችግር የሚያጋልጡ በምሽት መብራት የሌላቸው ጨለማ ቦታዎች ያሉባቸው ዩኒቨርስቲዎች መኖራቸው፣

13. አቅጣጫ ጠቋሚ ሰሌዳና የሀሳብ መስጫ ሳጥኖች/ Suggestion Boxes/ የሌሉባቸው ዩኒቨርስቲዎች መኖራቸው፣

14. በተማሪዎች ላይ የሚታየውን የሥነ-ምግባር ችግር ለመቅረፍ እንዲቻል የውስጥና የውጪ ባለድርሻ አካላትን በጋራ የሚያሳትፍ መድረክ የሌላቸው ዩኒቨርስቲዎች መኖራቸው፣

15. በአካባቢያቸው ላይ የጫት፣ የሺሻ፣ የመጠጥ፣ የጭፈራ እና የዝሙት ቤቶች ያሉባቸው ዩኒቨርሲቲዎች መኖራቸው፣

በአጠቃላይ የማስፈጸሚያ ህጎችን ደንብና መመሪያዎችን በማዘጋጀትና ለሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላት ስለአተገባበሩ ግንዛቤውን እንዲያገኙና ሰነዱም እንዲደርሳቸው ተደርጎ በአፋጣኝ ወደ ትግበራ ካልተገባ፣ የቅንጅት ስራዎች ካልተጠናከሩና ጠንካራ የክትትል እና የቁጥጥር ስርዓት ካልተዘረጋ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተግባር ስኬታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶችና ድክመቶች ሊያርሙና በአጠቃላይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሥነ-ምግባር የታነጸ የተማረ የሰው ኃይል ለማፍራት የሚያደርጉትን ጥረት ያግዛሉ ተብሎ የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች

- በመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ለሚገኙ የኢኮኖሚ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የሚደረገውን ድጋፍ አሰጣጥ የተቀናጀና ፍትሐዊ ለማድረግ የሚያስችል የመመልመያ መስፈርት ማዘጋጀትና መስፈርቱን የሚያሟሉ ተማሪዎች ድጋፉን እንዲያገኙ ማድረግ እንዲሁም የመስፈርቱ አተገባበር ስላስከተለው ለውጥ በየጊዜው ግምገማ በማድረግ ክፍተቶችን ለመሙላት ሰነዱን በመከለስ ወቅታዊ ማድረግ ይገባል፡፡

- የማጠናከሪያ ትምህርት (ቲቶሪያል ክላስ) አተገባበር በሁሉም ዩኒቨርስቲዎች ወጥነት እንዲኖረው የአተገባበር መመሪያ በትምህርት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ ለየዩኒቨርስቲዎቹ ሊሰራጭና ተግባራዊነቱ ሊረጋገጥ፣ ዩኒቨርስቲዎችም በተመረጡ ትምህርቶች/ኮርሶች ላይ ሞጁል በማዘጋጀት የትምህርት ድጋፉ በሞጁሉ መሰረት መሰጠቱን ክትትል ሊደረግና ተማሪዎቹም ትምህርቱን እንዲከታተሉ ለማድረግ በጠቀሜታው ዙሪያ ግንዛቤ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በተጨማሪም መምህራን ከመደበኛው የማስተማሪያ ሰዓት ውጪ በተጨማሪ ሰዓት ለሚሰጡት የማጠናከሪያ ትምህርት ማበረታቻዎችን በመስጠት በማስተማር ስራቸው ላይ እንዲገኙ ቢደረግ መልካም ነው፡፡

- ተማሪዎች በተቋም ቆይታቸው ሊያጋጥማቸው ከሚችሉ ተቋማዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ፣ ጾታዊና ሥነ-ምግባራዊ ችግሮች ለመታደግ እንዲቻል ስለ አጠናን ዘዴ፣ በክፍል ውስጥ የሚያደርጉትን ተሳትፎ ስለማሳደግ፣ ስለሥነ-ተዋልዶ ጤና አጠባበቅ፣ ስለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና ለአደገኛ ሱሶች ተጋላጭ እንዳይሆኑ ስለሚያስከትሉት አሉታዊ ተጽዕኖዎች እና በዋና ዋና የህይወት ክህሎቶች ላይ በቀላሉ ሊረዱትና እየተዝናኑ ሊማሩበት በሚያስችል መልኩ የሚዘጋጁ የመዝናኛ መድረኮች፣ የሚሰራጩ የህትመት ሥራዎች፣ የመምህራንና የተማሪዎችን የህይወት ተሞክሮ ማካፈል እና በጥናት የተደገፉ ፅሁፎችና ፊልሞችን በማቅረብ እስካሁን ያሉ አበረታች ጅምር ስራዎችን በማጠናከር ሁሉንም ተማሪዎች ሊያሳትፍ በሚችል መልኩ ሊቀርብላቸው ይገባል፡፡

- ሴት ተማሪዎች ለጾታዊ ጥቃት እንዳይጋለጡ ለማድረግ የተቀራረበ የሴትና የወንድ ተማሪዎች መኖሪያ /ዶርም/ ባለባቸው የየዩኒቨርስቲው ካምፓሶች መኖሪያቸው በአጥር

ሊከለል፣ ጥበቃ ሊደረግ፣ ለሴት ተማሪዎች ቢያንስ የማንበቢያና የቴሌቪዥን /TV room/ አገልግሎት መስጫ ለብቻቸው እንዲያገኙ ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ለአስነዋሪ ተግባር እንዳይጋልጡ በየዩኒቨርስቲዎቹ ቅጥር ግቢ ውስጥ በምሽት ጨለማ የሆኑ ቦታዎች የኤሌክትሪክ ብርሃን ሊኖራቸው ይገባል፡፡

- ተማሪዎች መዝናኛዎችንና የተለያዩ አገልግሎቶችን ፍለጋ ከግቢው ሲወጡ በዛው ለአልባሌ ተግባር እንዳይጋለጡና ትርፍ ጊዜያቸውን በዩኒቨርስቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዲያሳልፉ ለማድረግ  በየዩኒቨርስቲው በሚገኙ ካምፓሶች የተማሪውን ቁጥር ያገናዘበ የመዝናኛ ማዕከላትንና የተለያዩ አገልግሎት መስጫዎችን በማብዛትና በማጠናከር ተማሪዎች ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠርላቸው ሊደረግ ይገባል፡፡  የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችን ለሴትኛ አዳሪነት ተግባር አሳልፈው የሚሰጡ  ደላሎች (ተማሪዎችም ሆኑ ሌሎች አካላት) ሲገኙ መጠቆም እንዲችሉ  ተማሪዎችን ማበረታታትና ለጠቋሚዎቹ የህግ ከለላ መስጠት፣ ደላሎቹም ሲገኙ ህጋዊ እርምጃ በማስወሰድ የተወሰደውን እርምጃ ለህብረተሰቡ ይፋ ማድረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎችን ፎቶ ይዘው ለወሲብ ንግድ የሚያስማሩ ሆቴሎች የመኖራቸውን እርግጠኛነት በአካባቢው ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት (የከተማ አስተዳደር፣ የፖሊስ አካላት፣ የማዘጋጃ ቤቶችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች) ጋር ተቀናጅቶ በመስራት ማጣራትና እንደ ሀገር (ግለሰብ) የሚያደርሰው ኪሳራ ከፍተኛ በመሆኑ የተለየ ትኩረት ተሰጥቶት ሴት ተማሪዎችን መታደግ የሚቻልበት ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡
- ተማሪዎች በተቋሙ ውስጥ የሚሰጡትን  አገልግሎቶችና አድራሻቸውን በቀላሉ እንዲያገኙ ለማስቻል የአገልግሎቶቹን አይነትና የቢሮ ቁጥር የያዘ አቅጣጫ ጠቋሚ በግቢው መግቢያ እና በየአገልግሎት መስጫው አካባቢ ሊኖር፣ የሀሳብ መስጫ ሳጥኖችም /Suggestion Boxes/ በየዩኒቨርስቲው  ካምፓሶች ቅጥር ግቢ በተለያየ ስፍራ ተቀምጦ ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ሊደረግበት፣ ለሚያነሱትም ተገቢ ጥያቄና ቅሬታ የሚመለከተው አካል ወቅታዊ መፍትሄዎች ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
- በየዩኒቨርስቲው በሚገኙ ካምፓሶች ተማሪን በቅርበት መርዳትና መፍትሔ ማምጣት የሚችሉ በተለይ የሥርዓተ-ጾታ፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስና የሥነ-ምግባር ጽ/ቤቶችና የሥነ-ልቦና ባለሙያዎች ሊኖሩ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ለሁሉም የየዩኒቨርስቲው ሰራተኞች የስራ መዘርዝር(Job description)ና ለየሥራ ክፍሎቹ ደግሞ የሥራ መመሪያ ተዘጋጅቶ ሊሰጣቸውና አፈጻጸማቸውም ሊገመገም ይገባል፡፡ የሚቻል ሆኖ ሲገኝ የሥነ-ልቦና አማካሪ


ባለሙያዎች ጾታን ያማከሉ ቢሆኑ በተመሳሳይ ወይም በተቃራኒ ጾታ ለመገልገል ለሚመርጡ ተማሪዎች እድሉን ይከፍታል፡፡

- በሁሉም ዩኒቨርስቲዎች በወጥነት የሚተገበር የመምህራን የሥነ-ምግባር ደንብና መመሪያ ሊዘጋጅ፣ ግንዛቤ ሊሰጥበትና ሁሉም መምህራን እንዲደርሳቸው ሊደረግ እንዲሁም ተግባራዊ በማያደርጉት መምህራን ላይ የሥነ-ምግባር ጉድለቶችን ሊመረምርና ለእርምጃ ሊያቀርብ የሚችል ጠንካራ ኮሚቴ በማቋቋም ተገቢና አፋጣኝ ውሳኔ መስጠትና የተወሰደው እርምጃ ለተቋሙ ማህበረሰብ ይፋ የሚደረግበት አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡ እንዲሁም የተማሪዎች የሥነ-ምግባር ደንብና መመሪያው ግንዛቤ የማግኘት ክፍተት እንዳይኖር የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ግንዛቤውን በመስጠት ሁልጊዜ እንዲያስታውሱና እንዲተገብሩት ሊደረግ ይገባል፡፡
- በየዩኒቨርስቲው የሚገኙ የሥርዓተ-ጾታ፣ የሥነ-ምግባርና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤቶች፣ የተማሪዎች አገልግሎትና የጥበቃ ሰራተኞች በተማሪዎች ላይ የሚታዩትን ችግሮች በጋራ ለመፍታት በቅንጅት የሚሰሩበት መድረክ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በዚህ ጉዳይ በባህር-ዳር ዩኒቨርስቲ የታየው በቅንጅት የመስራት ጅምር ስራ የሚበረታታና ሌሎችም ዩኒቨርስቲዎች ቢተገብሩትና ያመጣውን ለውጥ ቢገመግሙ በተማሪዎች ላይ የሚታየውን የሥነ-ምግባር ችግር ለመቅረፍ ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል፡፡
- በተማሪዎች ላይ የሚደርሱትን አካባቢያዊ ጠንቆች ለማስወገድ የውጪ ባለድርሻ አካላትን (የከተማ መስተዳድሮችን፣ የከተማውን ፖሊስ መምሪያ፣ በጎ ተፅእኖ ያሳድራሉ ተብሎ የታመነባቸውን የሐይማኖት ሰዎችና የህብረተሰብ ክፍሎችን) የሚያሳትፍ መድረክ በየጊዜው በማዘጋጀት ማወያየት፣ በተገኙ ችግሮች ላይ እርምጃ መውሰድና ህብረተሰቡም ትውልድን ለማዳን የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ማሳሰብ ይገባል፡፡ በተለይ በየተቋሙ አካባቢ የሚታዩት የጫት፣ የሺሻ፣ የመጠጥ፣ የጭፈራና ለወሲብ ተግባር የሚውሉ ቤቶች ላይ ትኩረት ተሠጥቶት መሰራት አለበት፡፡
- በመጨረሻም የትምህርት ሚኒስቴር፣ እና በናሙና ተመርጠው የመረጃ ማሰባሰብ ሥራ የተሰራባቸው የዲላ፣ የሀዋሳ፣ የጎንደርና የባህር-ዳር ዩኒቨርሰቲ የስራ ኃላፊዎች፣ ሠራተኞችና ተማሪዎች እንዲሁም ዩኒቨርስቲዎቹ በሚገኙበት ከተሞች ያሉ የከተማ አስተዳደርና ፖሊስ መምሪያ በኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

አባሪ 1

# የትምህርት ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር /2003 ዓ.ም./

አባሪ 1



# አባሪ 2

## የኦዲት መገምገሚያ መስፈርቶችና የሚፈለጉ መረጃዎች

## (Evaluative Criteria and Information Required)

ኦዲት ተደራጊ፣ የትምህርት ሚኒስቴር

የኦዲት አካባቢ፣ በመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚገኙ ተማሪዎች ላይ የሚታዩ የሥነ-ምግባር ችግሮች እንዲሁም የሚገጥሟቸው ተቋማዊ እና አካባቢያዊ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን በተመለከተ

| የኦዲትየትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues& Sub Issues) | የኦዲትመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| 1. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በተማሪዎች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ችግሮችን ለማስቀረት አስገዳጅና ተጠያቂነትን የሚያጠናክሩ ፖሊሲዎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ሊወጡ፣ ለሌላው ተቋም አስተማሪ እንዲሆኑ የየዩኒቨርስቲዎቹ ደካማና መልካም ተሞክሮ መረጃዎች ሊሰባሰቡ፣ ሊጠናቀሩና ሊሰራጩ የሚችሉበትና የመረጃ ልውውጥ የሚኖርበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መሆኑን ማረጋገጥ፣ | 1.1 ለተማሪዎች የሥነ-ምግባር ደንብና መመሪያ ሊዘጋጅና ግንዛቤ ሊሰጥበት እንዲሁም መምህራን የሚተዳደሩበት የሥነ-ምግባር ደንብና የዲሲፕሊን መመሪያ ተዘጋጅቶ ለሁሉም መምህራን ሊሰራጭና ስለተግባራዊነቱም ክትትል ሊደረግበት ይገባል፡፡<br>/ |
| | 1.2 በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ሴት ተማሪዎች ደህንነት የተጠበቀ እንዲሆን በሥርዓተ-ጾታ ዙሪያ የሚወጡት መመሪያዎች ተጠያቂነትን የሚያጠናክሩና የሚተገበሩ መሆን አለባቸው:: |
| | 1.3 ትምህርት ሚኒስቴር በሁሉም ዩኒቨርስቲዎች የሚተገበር የተሻለና ወጥ አሰራር እንዲኖር ለማድረግ ከተለያዩ የውይይት መድረኮችና የአፈጻጸም ሪፖርቶች የተገኙ በጎና ደካማ አሰራሮች የሚጠናቀሩበት፣ በመረጃነት የሚጠበቁበትና ጥሩው ተሞክሮ ተለይቶ ለሁሉም ዩኒቨርስቲዎች እንዲሰራጩ የሚደረግበት የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 1.4. የሥርዓተ-ጾታ፣ የሥነ-ምግባርና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤቶች በሚያከናውኗቸውን ስራዎች ዙሪያ ተማሪዎች መረጃን እንዲያገኙና የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር |

| የኦዲትየትኩረት አቅጣጫ<br>**(Audit Issues& Sub Issues)** | የኦዲትመመዘኛ መስፈርት<br>**(Evaluative Criteria)** |
| --- | --- |
| | የኤንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሲስተም (Internet, E-mail, web-site) መዘርጋትና ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡ |
| | 1.5. ሴት ተማሪዎች በመልካም ሥነ-ምግባር የተደገፈ እውቀትና የአላማ ፅናት እንዳይኖራቸው የሚያደርግ አጉል ዝንባሌ ሲታይባቸው ችግሮቹን ለማስወገድ በተለያዩ አካላት(ተማሪዎች፣አማካሪዎች፣ መምህራን…) ምክርና ተግሳፅ በመስጠት ከመጥፎ ሥነ-ምግባር እንዲታቀቡ ማድረግ ይገባል፡፡ |
| **2. ተማሪዎች በዩኒቨርስቲ ግቢ ውስጥ ደህንነታቸው እንዲጠበቅ፣ ወደ አልተፈለገ ቦታ እንዳይሄዱና በትምህርታቸው ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ለማድረግ የሚያስችል አገልግሎትበግቢ ውስጥ የሚያገኙ መሆኑን ማረጋገጥ፣** | |
| **2.1ሴት ተማሪዎች በዩኒቨርስቲ ግቢ ውስጥ ደህንነታቸው እየተጠበቀ መሆኑን ማጣራት፣** | 2.1.1. የሴትና የወንድ ተማሪዎች ማደሪያ/ዶርም/ የተራራቀ፣ በአጥር የተከለለ ሊሆንና የሴት ተማሪዎች ማደሪያ ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል፡፡ |
| | 2.1.2. በሴት ተማሪዎች ላይ ጾታዊ ጥቃት የሚያደርሱ መምህራንን፣ ተማሪዎችን፣ የዩኒቨርስቲ ሠራተኞችንና ሌሎች አካላትን ተከታትሎ ህጋዊ እርምጃ መውሰድ ይገባል፡፡ |
| | 2.1.3. ለሴት ተማሪዎች በዶርማቸው አካባቢ የቤተ-መጽሐፍት፣ የኢንተርኔትና የቴሌቪዥን /TV room/ አገልግሎት መስጫ ክፍል ለብቻቸው ሊኖራቸው ይገባል፡፡ |
| | 2.1.4. ሴት ተማሪዎች ያጋጠሟቸውን ችግሮች እርስ በርስ ተወያይተው የሚፈቱበት የሴት ተማሪዎች ሕብረት(ማህበር) በዩኒቨርስቲው ግቢ ውስጥ ሊኖርና ስራውን በአግባቡ እንዲወጣ ድጋፍ ሊደረግለት ይገባል፡፡ |
| | 2.1.5. ተማሪዎችን ለመጥፎ ሥነ-ምግባር እንዳያጋልጡ በየዩኒቨርስቲዎቹ ቅጥር ግቢ ውስጥ በምሽት ጨለማ የሆኑ ሁሉም ቦታዎች የኤሌክትሪክ ብርሃን ሊኖራቸው ይገባል፡፡ |
| | 2.1.6. የወሲብ ስሜት ቀስቃሽ የሆኑ ፊልሞች፣ ሥነ-ጽሑፎች፣ መጽሔቶች፣አለባበሶችና ድረ-ገጾች በዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዳይተገበሩ የሚከለክል ህግ ሊወጣና ድርጊቱን በሚፈጽሙ አካላት ላይ ክትትል እየተደረገ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ |
| | 2.1.7. አካል ጉዳተኛ የሆኑ ሴት ተማሪዎች በቀላሉ ለወሲብ ጥቃት እንዳይጋለጡ ለማድረግ ከሌሎች በተለየ ጥበቃና ክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ |
| | 2.1.8. ፈተናን እንደመቅጫ መሳሪያ የሚጠቀሙ፣ ውጤት አሰጣጣቸው አድሎአዊ የሆነ፣ ሴት ተማሪዎችን ለትምህርት ውጤትም ሆነ ለተለያዩ የትምህርት ተግባራት ወሲብን እንደቅድመ ሁኔታ የሚጠይቁ መምህራንን ተከታትሎ ተገቢ እርምጃ መውሰድ ይገባል፡፡ |
| | 2.1.9. አድሎአዊ ውጤት አሰጣጥን ለማስቀረት ሁሉም |

| የኦዲትየትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues& Sub Issues) | የኦዲትመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | መምህራን የተማሪዎችን ውጤት በማስታወቂያ ቦርድ ላይ ከመለጠፋቸው በፊት የፈተና ውጤታቸውንና ተያያዥነት ያላቸውን የመመዘኛ ሰነዶች ሊያሳያቸውና በውጤታቸው ላይ ቅሬታ ካለ በግልጽ ሊያነጋግሩአቸው ይገባል፡፡ |
| 2.2 ተማሪዎች ወደ አልተፈለገ ቦታ እንዳይሄዱና በትምህርታቸውላይ ብቻ እንዲያተኩሩ የሚያደርግ ሥራ በዩኒቨርስቲዎች እየተሰራ መሆኑን ማጣራት፣ | 2.2.1. ጥሩ ውጤት ለሚያመጡ፣ በመልካም ሥነ-ምግባር ለታነጹ፣ የሕይወት ተሞክሮአቸውን በማካፈል ንቁ ተሳታፊ ለሆኑ ተማሪዎች ለሌሎች ምሳሌ (role models) እንዲሆኑ ዕውቅና እንዲያገኙ ማድረግና የማበረታቻ ሽልማቶችን መስጠት ይገባል፡፡ |
| | 2.2.2. አስተያየት መስጫ ሳጥኖች/ Suggestion Boxes/ በዩኒቨርስቲው ቅጥር ግቢ በተለያየ ስፍራ እንዲኖር ሊደረግ፣ ተማሪዎችም በአስተያየት መስጫ ሳጥን ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ሊበረታቱና ለሚያነሱት ተገቢ ጥያቄና ቅሬታ የሚመለከተው አካል ወቅታዊ መፍትሄዎች ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ |
| - | 2.2.3. በየዩኒቨርስቲው የሚገኙ የመዝናኛ ማዕከላት የሚሰጡትን አገልግሎቶች (የሙዚቃ፣ የድራማ፣ የሥነ-ጽሁፍ ምሽት የክርክር መድረክ፣ የፓናል ውይይት፣...) በማብዛትና ከውጭ በሚገኙ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ዕርዳታ በማጠናከር ተማሪዎች ትርፍ ጊዜያቸውን በዩኒቨርስቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዲያሳልፉ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 2.2.4. የከተማ መስተዳድሮች፣ ማዘጋጃ ቤቶችና ክፍለ ከተሞች በዩኒቨርሲቲዎች አካባቢ የጫት፣ የሺሻ፣ የመጠጥ፣ የጭፈራ እና የመሳሰሉት ቤቶች እንዳይሰሩ በቅንጅት ሊከላከሉና ለጎጂ ሱስ የሚያጋልጡ ነገሮችን በአካባቢው ሲሸጡ በሚገኙ ሰዎች ላይ የፓሊስ አካላት ጥብቅ ቁጥጥር ሊያደርጉ ይገባል፡፡ |
| | 2.2.5. የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች በተማሪዎች ላይ የሚደርሱትን ማህበራዊ ጠንቆች ለማስወገድ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተጠናከረ ግንኙነት በመፍጠር ተቀራርቦ ለመሥራት የሚያስችል የውይይት መድረክ ሊያዘጋጁ ይገባል:: |
| | 2.2.6. የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎችን ለሴትኛ አዳሪነት ተግባር አሳልፈው የሚሰጡ ደላሎች(ተማሪዎችም ሆኑ ሌሎችአካላት) በተማሪዎች ጠቋሚነት እንዲጋለጡ ለጠቋሚዎቹ ማበረታቻ መስጠትና በደላሎቹም ላይ በቂ ክትትል በማድረግ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 2.2.7. ተማሪዎች በክፍል ውስጥ መገኘት በሚገባቸው ሰዓት መገኘታቸውን ለማረጋገጥ ሁሉም መምህራን የክፍል መቆጣጠሪያ (class attendance) ወጥ በሆነ መልኩ ሊይዙ፣ መምህራንም በተሰጣቸው ክፍለ ጊዜ መሰረት በክፍሉ ውስጥ መገኘታቸው ሊረጋገጥና በማይገኙ ተማሪዎችና መምህራን ላይ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ |
| | 2.2.8. በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ ተማሪዎች ማህበራዊ፣ ኢኮኖማዊ ሆነ ሥነ-ልቦናዊ ችግሮች |

| የኦዲትየትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues& Sub Issues) | የኦዲትመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | ሲያጋጥማቸው የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ጾታን ያማከሉ፣ ለሥራው ብቃትና ፍላጎት ያላቸው ለዚህ አገልግሎት ብቻ የተመደቡ አማካሪዎች ሊኖሩ ይገባል፡፡ |
| | 2.2.9. ተማሪዎች በተቋሙ ውስጥ የሚሰጡትን አገልግሎቶች አድራሻ በቀላሉ እንዲያገኙ ለማስቻል የአገልግሎቶቹን አይነትና የቢሮ ቁጥር የያዘ አቅጣጫ ጠቋሚ በግቢው መግቢያ እና በአገልግሎት መስጫው አካባቢ ሊኖር ይገባል፡፡ |
| **3. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በዩኒቨርስቲ ግቢ ውስጥ ሊደርሱባቸው ከሚችሉ ማህበራዊ፣ ተቋማዊ፣ ሥነ-ልቦናዊና ጾታዊ ችግሮች ለመታደግ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት እየተወጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣** | |
| **3.1. የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎች ሊደርስባቸው ከሚችል ሥነ-ልቦናዊ፣ ማህበራዊ፣ ጾታዊና ሥነ-ምግባራዊ ችግሮች ለመከላከል የተደራጀና በአግባቡ ሥራውን መወጣት የሚችል የሥርዓተ-ጾታ፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና የሥነ-ምግባር ጽ/ቤት መኖሩን ማጣራት፣** | 3.1.1. እያንዳንዱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሥርዓተ-ጾታ፣ የሥነ-ምግባር እና የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ጽ/ቤት ሊኖረውና የሰው ኃይሉም የተሟላ፣ሥራውን ለመሥራት የሚያስችል የሙያ ብቃትና ቁርጠኝነት ያለው መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 3.1.2. የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሥርዓተ-ጾታ፣የሥነ-ምግባር እና የኤች.አይ. ቪ./ኤድስ ጽ/ቤቶች ዕቅዳቸውን የሚያሳኩበት ዓመታዊ በጀት ሊኖራቸውና በጀቱም ለታቀደለት አላማ ብቻ መዋሉ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 3.1.3. በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ የሚገኙ የሥርዓተ-ጾታና የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ጽ/ቤቶች ተልዕኮአቸውን በብቃት ለመወጣት የሚያስችል የፋይናንስ አቅም እንዲኖራቸው ከተለያዩ ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ጋር አጋርነት በመፍጠር የገንዘብ ድጋፍ ሊያገኙና የተገኘውንም ገንዘብ በዕቅዱ መሠረት በስራ ላይ ሊያውሉት ይገባል፡፡ |
| | 3.1.4. የሥርዓተ-ጾታ፣ የሥነ-ምግባርና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤት መዋቅር፣ የሠራተኛ የሥራ መዘርዝርና የሥራ መመሪያ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ |
| | 3.1.5. በዩኒቨርስቲው የሚገኙ የሥነ-ምግባር፣ የሥርዓተ-ጾታና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤቶች ቢሮ፣ የቢሮ ዕቃዎችና ሌሎች ለስራው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ሊሟሉላቸው ይገባል፡፡ |
| | 3.1.6. በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ የሚገኙ የሥርዓተ-ጾታና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤት ሠራተኞች የተለያዩ ማበረታቻዎችንና ወቅቱን የጠበቀ ከሥራው ጋር የሚያያዝ ሥልጠና በመስጠት በሥራ ገበታቸው ላይ |

| የኦዲትየትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues& Sub Issues) | የኦዲትመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | እንዲቆዩና ውጤታማ እንዲሆኑ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 3.1.7. በየዩኒቨርስቲው የሚገኙ ሥራ አመራሮች የሥርዓተ-ጾታን፣ የሥነ-ምግባርንና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤትን ሥራ አፈጻጸም ሊገመግሙና በተገኙ ክፍተቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡ |
| | 3.1.8. በየዩኒቨርስቲው የሚገኙ ዳይሬክተሮች ተማሪዎች በሚገጥማቸው ችግሮች ዙሪያ ከሥርዓተ-ጾታ፣ ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ከሥነ-ምግባር ጽ/ቤቶች ጋር በጋራ ሊሰሩና ሥራቸው በሥራ አመራሩ ሊገመገም ይገባል፡፡ |
| | 3.1.9. በየዩኒቨርስቲው የሚገኙ የሥርዓተ-ጾታ፣ የሥነ-ምግባር፣ የሕግ አገልግሎትና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤቶች በቅንጅት የሚሰሩበት መድረክ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ |
| | 3.1.10. ሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሥርዓተ-ጾታንና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሜንስትሪሚንግ ስራዎችን በአመታዊ እቅዳቸው ሊያስገቡትና አፈጻጸሙንም ሊከታተሉ ይገባል፡፡ |
| | 3.1.11. ትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሥራ አመራሮች በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ በሥርዓተ-ጾታናበሥነ-ምግባር ጽ/ቤት ዙሪያ እየሰሩ ያሉትን ሥራና የተገኘውን ውጤት ገምግሞ ክፍተቶች ካሉ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ |
| **3.2 በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤቶች የተሟላ አገልገሎት እየሰጡ መሆኑን ማረጋገጥ፣** | 3.2.1. በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ ተማሪዎች በሙሉ ፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ምርመራ እንዲያደርጉ የሚያበረታታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የምክርናየምርመራ አገልግሎት ማዕከል ሊኖርና ማዕከሉም የተሟላ የህክምና ቁሳቁስ ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 3.2.2. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ውስጥ የሚገኝ ተማሪዎች ከሚደርስባቸው የሥነ-ልቦና፣ የጤና እና የኢኮኖሚ ችግር ለመታደግ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጽ/ቤቱ በኩል በቂ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ |
| | 3.2.3.በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ የፀረ-ኤድስ ክለብ፣ ሚኒ ሚዲያና የመረጃ ዴስክ ሊኖር ይገባል፡፡ |
| **3.3 በየዩኒቨርስቲው የሚገኙ የሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤቶች የኢኮኖሚ ድጋፍ ማግኘት ላለባቸውተማሪዎች አግባብ ባልሆነ መንገድ ገቢ ለማግኘት ሲሉ ለአደጋ እንዳይጋለጡ የገንዘብ ድጋፍ በማድረግና በአካዳሚክ ትምህርታቸው ወደ ኋላ ለቀሩ ከትምህርት ሰዓት ውጭ የማጠናከሪያ ትምህርት በመስጠት አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ መደረጉን ማረጋገጥ፣** | 3.3.1. በሁሉም ዩኒቨርስቲዎች የኢኮኖሚ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ድጋፍ ሊደረግላቸው፣ ድጋፍ አሰጣጡም የተቀናጀ፣ ህጋዊና ፍትሐዊ ሊሆንና ተቋማዊ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ሊዘረጋለት ይገባል፡፡ |
| | 3.3.2. በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የኢኮኖሚ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የመመልመያ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡ |
| | 3.3.3 በተዘጋጀው መስፈርት መሰረት እየተሰራ ስለመሆኑና በተማሪዎች የትምህርት ውጤት ላይ ስላስከተለው ለውጥ |

| የኦዲትየትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues& Sub Issues) | የኦዲትመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | ክትትልና ግምገማ በማድረግ ክፍተቶችን ለይቶ የመፍትሄ እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ አለበት፡፡ |
| | 3.3.4. የማጠናከሪያ ትምህርት ድጋፍ አሰጣጥ በተገቢው ሁኔታ እየተፈጸመ ስለመሆኑ እና ለሚያጋጥሙ ችግሮች የመፍትሄ ሀሳቦችን ለማምጣትና የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችል የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡ |
| | 3.3.5. በማጠናከሪያ ትምህርት አሰጣጥ ላይ በተማሪዎች ዘንድ ያሉ የአመለካከት ችግሮችን ለመቅረፍ ትምህርቱ ያመጣውን ለውጥ በመገምገም በጠቀሜታው ዙሪያ የግንዛቤ ስራ መስራትና የአጠናን፣ የአነባበብ ዘዴ እና በክፍል ውስጥ የሚያደርጉትን ተሳትፎ ለማሳደግ በዋና ዋና የህይወት ክህሎቶች ላይ የሥልጠና ሰነድ አዘጋጅቶ ሥልጠና መስጠት ይገባል፡፡ |
| | 3.3.6. የማጠናከሪያ ትምህርት ዋናው ትምህርት በተጀመረ በ15 ቀን ውስጥ እንዲጀመር፣ፈተናን መሰረት ያደረገና የፈተናን ወቅት የጠበቀ ብቻ እንዳይሆን መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊነቱ ክትትል ሊደረግበት ይገባል፡፡ |
| | 3.3.7. የማጠናከሪያ ትምህርቱ ወጥነት እንዲኖረው በተመረጡ ትምህርቶች/ኮርሶች ላይ ሞጁል ማዘጋጀትና የትምህርት ድጋፉም በሞጁሉ መሰረት መሰጠቱን ክትትል ማድረግ ይገባል፡፡ |
| | 3.3.8. መምህራን ከመደበኛው የማስተማሪያ ሰዓት ውጪ በተጨማሪ ሰዓት ለሚሰጡት የማጠናከሪያ ትምህርት፣ ትምህርት ሚኒስቴር ባወጣው የአከፋፈል ሥርዓት መሰረት በመክፈልና በተማሪዎች ላይ ባስመዘገቡት ውጤትና ባደረጉት ጥረት ልክማበረታቻዎችበመስጠት የማጠናከሪያ ትምህርቱን ዘላቂነት ማረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| **3.4በተማሪዎች ላይ በዩኒቨርስቲ ግቢ ውስጥ ሊደርሱ ስለሚችሉ ማህበራዊ፣ ተቋማዊ፣ ሥነ-ልቦናዊና ጾታዊ ችግሮች ግንዛቤ ማስጨበጫ እየተሰጠ መሆኑን ማጣራት፣** | 3.4.1. ጾታዊ ትንኮሳ የሚደርስባቸው ሴት ተማሪዎች ጥቃቱ በደረሰባቸው ሰዓት በተጨባጭ መረጃ ችግራቸውን እንዲያሳውቁ ችግሩ ከመድረሱ በፊት በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ |
| | 3.4.2 ተማሪዎች ሊደርሱባቸው ስለሚችሉ ተቋማዊ፣ ሥነ-ልቦናዊና ጾታዊ ችግሮች በቀላሉ ሊረዱትና እየተዝናኑ ሊማሩበት በሚያስችል መልኩ የሚዘጋጁና የሚሰራጩ የህትመት ሥራዎች ሊኖሩ ይገባል፡፡ |
| | 3.4.3. በየተቋሙ የሚገኙ ሴት ተማሪዎች ላልተፈለገ እርግዝናና ውርጃ እንዳይጋለጡ በሥነ-ተዋልዶ ጤና አጠባበቅ ዙሪያ ከሚሰሩ የጤና ድርጅቶች ጋር በመተባበር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ |
| | 3.4.4. ተማሪዎች በዩኒቨርስቲ ቆይታቸው ተቋማዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ስነልቦናዊ ችግሮች ቢገጥማቸው እንዴት ማለፍ እንደሚችሉ መምህራን ከህይወት ተሞክሮቻቸው ተነስተው ለተማሪዎች የሚያስተምሩበት መድረክ ሊዘጋጅ ይገባል፡ |
| | 3.4.5. በከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚገኙ ተማሪዎች ለአደገኛ ሱሶች ተጋላጭ እንዳይሆኑፖሊሲ ሊቀረጽና የመዝናኛ |

| የኦዲትየትኩረት አቅጣጫ<br>(Audit Issues& Sub Issues) | የኦዲትመመዘኛ መስፈርት<br>(Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | መድረኮች እየተዘጋጁ ስለሚያስከትሉት አሉታዊ ተጽእኖ በጥናት የተደገፉ ፅሁፎችና ፊልሞች ሊቀርቡ ይገባል፡፡ |
| | 3.4.6. አዲስ ለሚገቡ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲው ውስጥ ሊገጥማቸው ስለሚችል ማህበራዊ፣ ተቋማዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ሥነ-ልቦናዊና ጾታዊ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው ቅድሚያ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በቅበላ ወቅት በቂ ገለጻ መስጠትና ቀድመው ከገቡ ተማሪዎች ተሞክሮ እንዲያገኙ ማድረግ ይገባል፡፡ |
| | 3.4.7 በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በመጀመሪያ ዓመት በሚሰጡ ትምህርቶች/ኮርሶች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ሥርዓተ-ጾታ በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ሊካተቱ ይገባል፡፡ |
| | 3.4.8. ተገቢ ያልሆነ(ኢ-ሥነምግባራዊ) የመምህርና የተማሪ ግንኙነት ሲኖር ተማሪዎች ይህንን ጉዳይ ለሥነ-ምግባር ጽ/ቤት እንዲያመለክቱ ማበረታታት ይገባል፡፡ |

# በኦዲቱ ወቅት የተከለሱ መረጃዎች

**ለመምህራንና ተማሪዎች የሚያገለግል የሥነ-ምግባር ደንብና መመሪያን በተመለከተ፣**

- በሀዋሳ በየዓመቱ በተደጋጋሚ በተማሪው ላይ የስነ-ምግባር ግድፈቶች መታየታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜም መልካቸውን እየቀያየሩ መምጣታቸው አንዱ ችግር መሆኑን (የሀዋሳ የ2004 የሥነ-ምግባር ጽ/ቤት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት)

**መምህራን የሚጠበቅባቸውን ተግባርና ኃላፊነት መወጣታቸውን በተመለከተ፣**

- በጎንደር ዩኒቨርስቲ ረቡዕ ታህሳስ 24 ቀን 2005 ዓ.ም. ሪፖርተር ጋዜጣ ባወጣው እትም የባዮ ቴክኖሎጂ ሁለተኛ አመት ተማሪን እንዲያስጠኗት በዲፓርመንቱ የተመደቡት የዩኒቨርስቲው የተማሪዎች ዲን፣ ተማሪዋ ባቀረበችባቸው የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ተጠርጥረው እንደታሰሩ፣
- በዲላ አንዲት የሁለተኛ አመት የነርሲንግ ኘሮግራም ተማሪ አንድ መምህር አጥሬራ ይዘሻል በሚል ሰበብ ፈተናዋን ሳትጨርስ እንደነጠቃት፣ በሌላ ፈተና ደግሞ ለተማሪ አሳይተሻል በሚል እንደፈረመባትና ማርክ እንደቀነሰ እንዲሁም በርካታ ለወሲብ የሚጋብዘ መልክቶችን እንደላከ፣ (የዲላ ዩኒቨርስቲ ከሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤት ለጤና ሳይንስ ጽ/ቤት የተፃፈ ደብዳቤ ቁጥር ጀ/479/15)
- በሀዋሳ፣ በጅማ፣ በመቀሌ፣ በጎንደርና በሐሮማያ ዩኒቨርስቲዎች በትምህርታቸው ደከም ያሉ ሴት ተማሪዎች ጥሩ ውጤት ለማምጣት ሲሉ ከአስተማሪዎቻቸው ጋር ለመተኛት እንደሚገደዱ፣ (የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ጥንቃቄ የጐደለው የወሲብ ባህሪያትና በተማሪዎች ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖ ላይ የተጠና ጥናት ገጽ 51)
- በባህር-ዳር በሁለተኛ ወሰነ ትምህርት ዘመን የሚስተናገዱ ተማሪዎችን ለይቶ የመኝታ አገልግሎት እንዲቀጥሉ ለማድረግ በኢንጅነሪግ እና በቢዝነስ ኢኮኖሚክስ ግቢ ማለፋቸውን የሚያስረዳ ግሬድ ሪፖርት ለሁሉም በወቅቱ ባለመስጠቱ ለሥራው እንቅፋት መፍጠሩን፣ (የባህር-ዳር ዩኒቨርስቲ የ2004 የተማሪዎች አገልግሎት የሥራ ሂደት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ገጽ 8)

**ከመደበኛ ትምህርት በተጨማሪ የሚሰጠውን የማጠናከሪያ ትምህርት(ቲቶሪያል ክላስ) በተመለከተ፣**

- በዲላ እና በሀዋሳ የዩኒቨርስቲ አመራሮች የማጠናከሪያ ትምህርት አሰጣጥ ሂደት ላይ ክትትል እና ድጋፍ ማነስ መኖሩን፣ (በትምህርት ሚኒስቴር የዲላና የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤቶች የክትትል ድጋፍ ሪፖርት)
- የዩኒቨርስቲ አመራሮች ለማጠናከሪያ ትምህርቱ በቂ ሀብት (የቁሳቁስና ገንዘብ) አለመመደባቸውና በቂ ክትትል አለማድረጋቸውን እንዲሁም መምህራን የማጠናከሪያ ትምህርት አሰጣጥ በትምህርት ፖሊሲው የተካተተ ቢሆንም ትምህሩቱን እንደ አንድ የሥራ አካል አድርገው አለማየታቸውን፣ (በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የማጠናከሪያ ትምህርት አሰጣጥ ዙሪያ የተዘጋጀ የአሠራር ማዕቀፍ ገጽ 4)
- በዲላ የማጠናከሪያ ትምህርት አሰጣጥን በተመለከተ ት/ቤቶች ከሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤት ጋር ተቀናጅተው ባለመሥራታቸው በትምህርት አሰጣጡም ሆነ የተማሪዎችን ተጠቃሚነትና ውጤታማነት ክትትል በመረጃ መለካት አለመቻሉንና ብዙ ሴት ተማሪዎች በተማሪ መማር ባለመፈለጋቸው ሥራው የተሣካ እንዳይሆን ማድረጉን፣ (የዲላ ዩኒቨርስቲ የሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤት የ2004 የዕቅድ አፈፃፀም)
- በባህር-ዳር በ2003 ትምህርቱ በሚሰጥበት ወቅት የተማሪዎች ያለመገኘት ችግር እንደነበረ፣ (የባህር-ዳር ዩኒቨርስቲ 2003 የሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት)
- በባህር-ዳር የማጠናከሪያ ትምህርት አሰጣጥ የፕሮግራም መጣበብና ቋሚ አለመሆን እንዲሁም በ2004 ዓ.ም.መምህራኖች በጊዜው ቲቶሪያል ያለመጀመር ችግር መታየቱን፣ (የባህር-ዳር ዩኒቨርስቲ የ2004 ዓ.ም. የ6ወር እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ገጽ 2

**የኢኮኖሚ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የተዘጋጀ የመመልመያ መስፈርት ስለመኖሩና ተግባራዊ ስለመደረጉ፣**

- በዲላ ወደ ጽ/ቤቱ የሚመጡት ሴትም ሆነ ወንድ ተማሪዎች አብዛኞቹ የገንዘብ እና የማቴሪያል ድጋፍ ፈልገው መሆኑን ሆኖም ዩኒቨርስቲው ካለምንም ለጋሽ ድርጅቶች እርዳታ ድጋፉን ስለሚሰጥ ካሉት ችግረኛ ተማሪዎች አንፃር እንኳን ወንዶች ሊካተቱ ሴቶችንም ማዳረስ እንዳልተቻለ፣ (የዲላ ዩኒቨርስቲ የሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤት የ2004 ዓ.ም. የ1ኛ ዓመት ዕቅድ ክንውን ሪፖርት)

- በሀዋሳ የመማሪያ ቁሳቁስ ድጋፍ ለሚሹ ሁሉም ተማሪዎች በአቅም ውስንነት የተነሳ የኢኮኖሚ ድጋፍ መስጠት አለመቻሉን፣ (የሀዋሳ የተማሪዎች ጉዳይ ጽ/ቤት የ2004 የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት)
- በሁሉም ዩኒቨርስቲ ድጋፍ ማግኘት ያለባቸው ተማሪዎችን ሙሉ በሙሉ ማዳረስ አለመቻላቸውንና ተማሪዎች ገቢ ማስገኛ ሥራዎች በግቢ ውስጥም ሆነ ከግቢ ውጭ እንዲፈልጉ መገደዳቸውን፣(የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚ/ር ከትምህርት ሚ/ር ጋር በመተባበር የኢኮኖሚ ድጋፍ አሰጣጥ ላይ የተጠና ጥናት ገጽ 1 እና 3 )

**<u>ለተማሪዎች በቂ የመዝናኛና የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት ስለመኖራቸው፣</u>**

- በዲላ ከሌሎች መሠል ዩኒቨርስቲዎች እንደተወሰደው ልምድ ለሴት ተማሪዎች ብቻ ተብሎ የተዘጋጀ ላይብረሪና ኢንተርኔት ክፍል ባለመኖሩ ሴቶች በነፃነት ማጥናት አለመቻላቸውን፣ (የዲላ ዩኒቨርስቲ የሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤት የ2004 ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት)
- በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሴት ተማሪዎች ለብቻቸው የማጥኛና የኢንተርኔት አገልግሎት መስጫ አለመኖሩን፣ (አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤት ሥራ አፈጻጸም ገጽ 8)
- በሀዋሳ፣ በጅማ፣ በመቀሌ፣ በጎንደርና በሐሮማያ ዩኒቨርስቲዎች ተማሪዎች የሚዝናኑበት የመዝናኛ እጥረት መኖሩን፣ (የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ጥንቃቄ የጐደለው የወሲብ ባህሪያትና በተማሪዎች ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖ ላይ የተጠና ጥናት ገጽ 30)
- በሀዋሳ ለሴት ተማሪዎች ማንበቢያ የሚሆን ክፍል እንዲዘጋጅ መጠየቁንና ነገር ግን ብሪቲሽ ካውንስል ሊያስረክባቸው ያቀደው መፅሐፍት በጉዞ ላይ መዘግየት አንዱ ችግር መሆኑን፣ (የሥርዓተ-ጾታ ጽ/ቤት ኃላፊ የ2004 የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ገጽ 2)
- በጎንደር የስፖርትና መዝናኛ ማቴሪያሎች ሲበላሹ መጠገን የሚችሉትን ለመጠገን የጥገና ባለሙያ እጥረት መኖሩን (በጎንደር ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች አገልግሎት የሥራ ሂደት የ2004 በጀት ዓመት ዕቅድ ክንውን ሪፖርት) ለማወቅ ተችሏል፡፡